# የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ፤በአዲስ አበባ በሚገኙ በአራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት
የቀረበ ጥናት

ለአማርኛ ማስተማር (TEAM) ኤም.ኤ.ዲግሪ
በከፊል ማሟያነት የተሰናዳ

ማስተዋል ውብቱ
ግንቦት፣ 1989 ዓ.ም.

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ፤
በአዲስ አበባ በሚገኙ በአራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች
የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት።


በ

ማስተዋል ውበቱ

ቋንቋ ጥናት ተቋም


የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| YONAS ADMASSU<br>አማካሪ | ፊርማ |
| RICHTER, Renate<br>ፈታኝ | ፊርማ |
| ZERIHUN Asfaw<br>ፈታኝ | ፊርማ |

## ምስጋና

አማካሪየ ዶክተር ዮናስ አድማሱ፣ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የዚህን ጥናት ረቂቅ በየጊዜው በጥንቃቄ በማንበብ፣ በማረምና ገንቢ አስተያየቶችን በመጠቆም ስለረዱኝ ከልብ አመሰግናቸዋልሁ።

ለስራየ መሳካት ከጎኔ ያልተለዩኝና በሞራል ያበረታቱኝ ጓደኞቼ አቶ ደመቀ ሙሉጌታ፣ አቶ መኰንን ባይህ እና አቶ ክፍሌ ሀብተማርያም ውለታቸው አይረሳኝም።

አቶ ዋለልኝ አድማሱ እና አቶ ተስፋሁን ዓለሙ የተለያዩ ስሌቶችን በመስራት ላደረጉልኝ እገዛ ምስጋናየ ይድረሳቸው። ወ/ሮ አዲስዓለም ሀብተሥላሴ ጥናቱን በኮምፒዩተር በጥንቃቄ ስላጻፈችልኝ አመሠግናታለሁ።

## አጠቃሎ (Abstract)

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማጥናት ነው:: ጥናቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ የመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በናሙናነት በተመረጡት አራት ትምህርት ቤቶች የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው:: ሁሉንም የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በጥናቱ ውስጥ ማካተትም ከአቅም በላይ ስለሆነ የተወሰኑ ተማሪዎች በናሙናነት ተመርጠው ጥናቱ ተካሂዷል::

ለጥናቱ ያገለገሉት የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎችም ለመምህራን የተሰራጨ የጽሑፍ መጠይቅ፣ የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ምልከታ እና አንብቦ የመረዳት ፈተና ናቸው:: መምህራንን የጽሑፍ መጠይቅ በማስሞላት፣ በክፍል ውስጥ በሚሰጠው የንባብ ትምህርት ላይ ምልከታ በማካሄድ፣ ለተጠኙ ተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ፈተና በመፈተን መረጃዎች ተሰባስበዋል:: የተሰበሰቡት መረጃዎችም ተተንትነዋል::

በጥናቱ የተገኘው ውጤት ጥናቱ የሚመለከታቸው ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያል:: ለተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆን ከሚጠቀሱት ውስጥ ዋነኞቹ የትምህርቱ አሰጣጥና የመማሪያ መጽሐፉ በዋነኛነት ይጠቀሳሉ:: ከመጠይቅ በተሰበሰቡት መረጃዎች መሠረት ንባብን ከማስተማሩና ከመማሪያ መጽሐፉ አኳያ ችግሮች አሉ:: በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የንባብ ትምህርት ተማሪዎችን እንደማያሳትፍ፣ አብዛኞቹ ተግባራት በመምህሩ እንደሚከናወኑ፣ ተማሪዎች በቂ ልምምድ እንደማያደርጉ በምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል:: የመማሪያ መጽሐፉም ይበልጥ የሚያተኩረው በንባብ ላይ ቢሆንም በአዘገጃጀቱ ችግር እንዳለበት መጠይቁን ከሞሉት መምህራን የተገኙት መረጃዎች ይጠቁማሉ::

በመጨረሻም በዚህ ጥናት ውስጥ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ሲባል ንባብን ለማስተማር የሚደረገው ጥረት ውጤታማ ይሆን ዘንድ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል::

# ማውጫ


ገጽ

ምስጋና i

አጠቃሎ ii

የሠንጠረዥ ዝርዝር

ምዕራፍ አንድ:- መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . 1

1.1 የጥናቱ ዳራ . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

1.2 የጥናቱ ዓላማ . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ . . . . . . . . . . . . . . . . 2

1.4 የጥናቱ ገደብ . . . . . . . . . . . . . . . . . 2

1.5 የቃላት ትርጉም እና ልዩ ልዩ ምልክቶች . . . . . . 3

1.5.1 የቃላት ትርጉም . . . . . . . . . . . . . . . 3

1.5.2 ልዩ ልዩ ምልክቶች . . . . . . . . . . . . . . 4

ምዕራፍ ሁለት:- ክለሣ ድርሳናት . . . . . . . . . . 5

2.1 የንባብ ትምህርት አቀራረብ . . . . . . . . . . . . . 5

2.2 አንብቦ የመረዳት ምንነት . . . . . . . . . . . . . . . 7

2.3 አንብቦ የመረዳት ችሎታን መመዘን . . . . . . . . . . 8

2.3.1 አንብቦ የመረዳት ፈተና ጥያቄ ዓይነቶች . . . 8

2.3.1.1 የምርጫ ጥያቄዎች (Multiple choice questions) . . . . . . . 9

2.3.1.2 ነጻ ጥያቄዎች (Open-ended questions) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 10

2.3.2 የጥሩ አንብቦ መረዳት ፈተና ባህሪያት . . . . . 11

2.3.3 አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥ . . . . 12

ምዕራፍ ሶስት:- የአጠናን ዘዴ . . . . . . . . . . . . . . . 14

3.1 የናሙና አመራረጥ . . . . . . . . . . . . . . . . . . 14

3.1.1 የትምህርት ቤቶች አመራረጥ . . . . . . . . . 14

3.1.2 የተማሪዎች አመራረጥ . . . . . . . . . . . . . 14

3.1.3 የመምህራን አመራረጥ . . . . . . . . . . . . 16

3.2 የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች . . . . . . . . . . . . . 17

3.2.1 ለመምህራን የተሰራጨ የጽሑፍ መጠይቅ . . . 17

3.2.2 የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ምልከታ . . . . 18

ገጽ

3.2.3 አንብቦ የመረዳት ፈተና . . . . . . . . . . . . . . . 19

3.2.3.1 አዘገጃጀት . . . . . . . . . . . . . . 19

3.2.3.2 አሰጣጥና አስተራረም . . . . . . . . . 20

ምዕራፍ አራት፡- የመረጃ ውጤት ትንተና እና ማብራሪያ . . . . . 22

4.1 የመረጃ ውጤት ትንተና . . . . . . . . . . . . . . . 22

4.1.1 ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና. . . 22

4.1.2 ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና . . . . . . 33

4.1.3 አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ትንተና . . . . . . . . . 37

4.1.3.1 የፆታ እና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝምድና ትንተና . . . . . . . . . . . . . 40

4.1.3.2 በአማርኛ አፍ የፈቱና ያልፈቱ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝምድና ትንተና. . 40

4.2 ማብራሪያ (Discussion) . . . . . . . . . . . . . . .. 41

ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያ እና አስተያየት . . . . . . . . . . . 46

5.1 ማጠቃለያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 46

5.2 አስተያየት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 48

ዋቢዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 50

የአባሪዎች ዝርዝር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 54

አባሪ 1፡- ለመምህራን የተሰራጨ የጽሑፍ መጠይቅ . . . . . 54

አባሪ 2፡- የምልከታ ዝርዝር (Observation sheet) . . . . 60

አባሪ 3፡- አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች . . . . . . . . . . . 61

ሀ. ፈተና አንድ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 61

ለ. ፈተና ሁለት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 65

አባሪ 4፡- ልዩ ልዩ ስሌቶች . . . . . . . . . . . . . . . . 68

ሀ. የፈተናዎች አስተማማኝነት ስሌት . . . . . . . . . . 68

ለ. የፈተናዎች ውጤት ግንኙነት ስሌት . . . . . . . . 68

ሐ. የፆታ እና አንብቦ የመረዳት ዝምድና ስሌት . . . . . 69

መ. የአፍ መፍቻ ቋንቋ እና አንብቦ የመረዳት ዝምድና ስሌት . . . . . . . . . . . . . . . .. 70

# የሠንጠረዦች ዝርዝር


| ሠንጠረዥ | | ገጽ |
| --- | --- | --- |
| 1 | አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ . . . . . . . . . . . . . . . | 13 |
| 2 | የናሙና ትምህርት ቤቶች፣ ምድቦችና ተማሪዎች . . . . . . | 16 |
| 3 | የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉ መምህራን ብዛት . . . . . . . . . | 16 |
| 4 | መጠይቁን የሞሉ መምህራን በፆታ . . . . . . . . . . . . | 22 |
| 5 | መጠይቁን የሞሉ መምህራን የትምህርት ደረጃ . . . . . . . | 22 |
| 6 | መጠይቁን የሞሉ መምህራን የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት. | 23 |
| 7 | መጠይቁን የሞሉ መምህራን የአገልግሎት ዘመን . .. . . . . . | 23 |
| 8 | የአማርኛ ትምህርቱ እና የመማሪያ መጽሐፉ የሚያተኩሩበት ክሂል . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | 24 |
| 9 | ለተማሪዎች መልመጃዎችን መስጠት እና ማረም . . . . . . | 25 |
| 10 | የተማሪዎች የክፍል ውስጥ የንባብ ልምምድ . . . . . . . . . | 26 |
| 11 | አንድ ምንባብ ከመነበቡ በፊት ስለምንባቡ ሐሳብ ስለመሰንዘሩ. | 28 |
| 12 | የአማርኛ ትምህርቱ እና የመማሪያ መጽሐፉ አንብቦ የመረዳት ችሎታን የማዳበር ብቃት . . . . . . . . . . . . . . . . . | 28 |
| 13 | የተማሪዎች የማንበብ ልምምድ እና ፍላጎት . . . . . . . . . | 30 |
| 14 | የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ . . . . . . . . . . . . | 32 |
| 15 | አንድ ምንባብ ከመነበቡ በፊት የሚከናወኑ ተግባራት . . . . . | 34 |
| 16 | አንድ ምንባብ ሲነበብ የሚከናወኑ ተግባራት . . . . . . . . . | 35 |
| 17 | አንድ ምንባብ ከተነበበ በኋላ የሚከናወኑ ተግባራት . . .. . . . . | 36 |
| 18 | በአራሚ አንድ የተገኘ የፈተና ውጤት . . . . . . . . . . . | 37 |
| 19 | በአራሚ ሁለት የተገኘ የፈተና ውጤት . . . . . . . . . . . | 38 |
| 20 | በአራሚ ሶስት የተገኘ የፈተና ውጤት . . . . . . . . . . . | 38 |
| 21 | በሶስቱ አራሚዎች የተገኘ አማካይ የፈተና ውጤት . . . . . . | 39 |
| 22 | የተጠኚ ተማሪዎች የውጤት ድግግሞሽ . . . . . . . . . . . | 39 |
| 23 | የፆታ እና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝምድና . . . . . . . . . | 40 |
| 24 | በአማርኛ አፍ የፈቱና ያልፈቱ ተማሪዎች እና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝምድና . . . . . . . . . . . . . . . . . . | 41 |

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

አማርኛ ራሱን የቻለ ትምህርት ሆኖ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚሰጠው የተለያዩ አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች ተነድፈውለት ነው፡፡ ከዓላማዎቹ ውስጥም አንዱ የተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ማዳበር የሚለው ነው (ት.ሚ፡ 1970፡ 1፣ 1984፡ 1 ያገናዝቧል)፡፡ የማንበብ ክሂል ከሚያካትታቸው ነጥቦች ውስጥም አንዱ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማዳበር ነው፡፡ ማንበብ ያለ መረዳት ፋይዳቢስ እንደሆነም ምሁራን ( Nuttal፡ 1982፣ Grellet 1981) ይገልጻሉ፡፡

በሀገራችን ውስጥ ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የተዘጋጁትን የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ስንመለከትም በውስጣቸው የሚገኙት አብዛኞቹ መልመጃዎች አንብቦ መረዳትን የሚመለከቱ እንደሆነ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን (በየነ 1985፣ ጌታቸው 1986) ያስገነዝባሉ፡፡ ከመልመጃዎች ውስጥ መልመጃ አንድ በሙሉ፣ መልመጃ ሁለት በከፊል፣ አልፎ አልፎ በመልመጃ ሦስት ሥር የተካተቱት ጥያቄዎች በአንብቦ መረዳት ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡

በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከሚሰጥባቸው ዓላማዎች ውስጥ አንዱ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማዳበር ነው፤ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ መልመጃዎችም የሚያተኩሩት በአንብቦ መረዳት ላይ ነው ቢባልም የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነ ምሁራን (ለምሳሌ፣ ተስፋዬ 1986፡9) ይጠቁማሉ፡፡ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መምህራንም የተማሪዎቻቸውን አንብቦ የመረዳት ችሎታ አነስተኛ መሆን በየአጋጣሚው ሲናገሩ ይሰማሉ፡፡

ይሁን እንጅ እስከዛሬ ድረስ "የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ነው፤ ተማሪዎቻችን አንብቦ የመረዳት ችግር አለባቸው፡፡" እያሉ ሀሳብ ከመሰንዘር አልፎ ጉዳዩን ጉዳየ ብሎ በመያዝ ጥናት አካሂዶ ያረጋገጠ የለም ማለት ይቻላል፡፡ ይህም "ለመሆኑ በእውነት እንደሚባለው የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ነውን ?" የሚል ጥያቄን ያስነሳል፡፡

---

*ደራሲያቸው ወይም አሳታሚያቸው በአማርኛ የተጻፉት ዘመናት አቆጣጠራቸው ዓ.ም. ሲሆን ደራሲያቸው ወይም አሳታሚያቸው በእንግሊዝኛ የተጻፉት ደግሞ አቆጣጠራቸው እ.ኤ.አ.ነው፡፡

የዚህ ጥናት አነሳስም ተጨባጭ የሆነ ምርምራዊ ጥናት አካሂዶ ይህን ጥያቄ መመለስ ነው፡፡ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በእርግጥ አነስተኛ ከሆነም፣ የዚህ ጥናት አንዱ ዓላማ የመፍትሄ ሐሳቦችን ለመሰንዘር ጭምር ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓላማ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማጥናት ነው፡፡ ጥናቱም የሚከተሉትን ዓላማዎች ከግብ ያደርሳል፡፡

1. የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑን ወይም አለመሆኑን መመርመር
2. የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከተማሪዎቹ ፆታ እና የአፍ መፍቻ ቋንቋ አንፃር መመርመር
3. የክፍሉን ውስጥ የንባብ ትምህርት መመርመር

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

1. የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ያስችላል፡፡
2. አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከፆታ እና ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር ያለውን ዝምድና ለመገንዘብ ያግዛል፡፡
3. በሁለተኛ ደረጃ የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር የሚያስችል መሆኑን ወይም አለመሆኑን ይጠቁማል፡፡
4. ከጥናቱ ውጤት በመነሳት (በእርግጥ እንደሚባለው የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ አነስተኛ ከሆነ) ለችግሩ የመፍትሄ ሐሳብ ይሰነዝራል፡፡
5. ከአንብቦ መረዳት ጋር በተያያዘ መልኩ ወደፊት ለሚደረጉ ሌሎች ጥናቶች የመነሻ ሀሳብ ይሰጣል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ገደብ

ይህ ጥናት የተካሄደው በአዲስ አበባ ውስጥ ከሚገኙ የመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ ነው፡፡ በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ የግል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በጥናቱ አልታቀፉም፡፡

የዚህም ምክንያቱ የግል ትምህርት ቤቶች ከትምህርት አሰጣጡ፣ ከማስተማሪያ መሳሪያዎቹ ብቃትና ጥራት፣ ከተማሪዎቹ ብዛት ወዘተ. አንጻር ከመንግሥት ትምህርት ቤቶች ይለያሉ ተብሎ በመታሰቡና ልዩነቱም በጥናቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል ከሚል ስጋት የተነሳ ነው::

በሁለተኛ ደረጃ ከሚገኙት የክፍል ደረጃዎች ውስጥም ለጥናቱ የተመረጠው 11ኛ ክፍል ነው:: 11ኛ ክፍል የተመረጠበት ምክንያትም ለጥናት አመችነት ያለው በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ክፍል በመሆኑ ነው:: በእርግጥ ከ11ኛ ክፍል ይልቅ 12ኛ ክፍል በከፍተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል:: ነገር ግን በ12ኛ ክፍል የሚማሩት ተማሪዎች በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሰጠውን መልቀቂያ ፈተና ወስደው ትምህርት ቤቶችን ቀደም ብለው ስለሚለቁ፣ ትምህርት ቤቶችን ከመልቀቃቸው በፊትም ለፈተናው ስለሚዘጋጁ ለጥናቱ አመች ሆነው አልተገኙም::

በናሙናነት በተመረጡት አራት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎችም በሙሉ በጥናቱ ውስጥ አልታቀፉም:: የዚህም ዋነኛው ምክንያት ከጥናቱ አድማስ የተነሳ ሁሉንም ተማሪዎች በጥናቱ ውስጥ ማካተት ባለመቻሉ ነው::

ከዚህ በተጨማሪም ጥናቱ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንጅ የማንበብ ፍጥነትን አይመለከትም:: የዚህም ምክንያቱ፣ የጥናቱ ዓላማ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት እንጅ የማንበብ ፍጥነት ማጥናት ባለመሆኑ ነው:: የንባብ ፍጥነት እንደ ንባብ ዓይነቱ ይለያያል:: የንባብ ዓይነቱ ደግሞ ጽሑፉ በሚነበብበት ዓላማ (purpose) ይወሰናል:: ለምሳሌ ከአንድ ጽሑፍ ዝርዝር መረጃዎችን ለማግኘት በጥልቀት የሚያነብና የጽሑፉን አጠቃላይ መልዕክት ለመገንዘብ በገረፍ-ገረፉ የሚያነብ ሰው የተለያየ የማንበብ ፍጥነት ይኖራቸዋል::

## 1.5 <u>የቃላት ትርጉም እና ልዩ ልዩ ምልክቶች መፍቻ</u>

### 1.5.1 <u>የቃላት ትርጉም</u>

ሀ. <u>አንብቦ መረዳት (reading comprehension)</u>:- አንድ ጽሑፍ ወይም ምንባብ የያዘውን አስፈላጊ መረጃ (information) ሁሉ በተቻለ መጠን መገንዘብን ይመለከታል (Grellet :1981:4):: በሌላ አገላለጽ አንብቦ መረዳት ጸሐፊው በጽሑፉ

ውስጥ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት (message) በተቻለ መጠን መገንዘብ መቻል ነው፡፡ (Nuttal፡ 1982፡ 5፣ Williams፡ 1993፡ 915፣ Jonathan 1971፡ 180)፡፡

ለ. <u>የችሎታ መለኪያ ፈተና (achievement test)</u>፡- በአንድ የተወሰነ የክፍል ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በተወሰነ የጊዜ ገደብ በተሰጣቸው ትምህርት አማካኝነት ችሎታቸው ከምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለመለካት የሚሰጥ ነው (Lewis፡ 1985፡ 113)፡፡

### 1.5.2 <u>ልዩ ልዩ ምልክቶች</u>

በዚህ ንኡስ ክፍል ሥር በዚህ ጥናት ውስጥ ከሚገኙት ልዩ ልዩ ምልክቶች ዋና ዋናዎቹ ይገለጻሉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| CF | = | comulative frequency |
| df | = | degree of freedom |
| $\Sigma$ | = | summation |
| $\Sigma x$ | = | summation of scores |
| $\Sigma x^2$ | = | summation of squared scores |
| F | = | frequency |
| N | = | number of subjects in the sample |
| p | = | significance level. |
| pr | = | correlation cofficient of the tests |
| r | = | reliability of the tests |
| sd | = | standard deviation |
| $sd^2$ | = | variance |
| $sd^2x_2$ | = | total variance |
| $sd^2y_1$ | = | variance of test one |
| $sd^2y_2$ | = | variance of test two |
| $s^2p$ | = | estimate variance of the population based up on the sample |
| t cal | = | the calculated value of t. |
| t tab | = | the tabulated value of t in the appropriate t distribution |
| X | = | scores |
| $\bar{X}$ | = | arthematic mean of scores |

## ምዕራፍ ሁለት

## ክለሣ ድርሳናት

### 2.1 የንባብ ትምህርት አቀራረብ

ከንባብ ትምህርት ዓላማዎች ውስጥ አንዱ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማዳበር እንደሆነ ቀደም ሲል በመግቢያው ውስጥ ተገልጿል፡፡ ይህ ዓላማ ከግብ እንዲደርስም የንባብ ትምህርቱ በምን መልክ ቢቀርብ ይሻላል? ፤ በትምህርቱ ወቅት መከናወን ያለባቸው ተግባራትስ ምን ምን ናቸው ? የሚሉት ጥያቄዎች በብዙ ምሁራን (Greenwood 1981፡ 93 - 101 ፣ Ellis 1980፡ 157 - 158፣ Williams 1983፡ 2) ይነሳሉ፡፡ የንባብ ትምህርቱ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያስችል ዘንድ የክፍል ውስጥ ክንውኑ በሦስት ደረጃዎች ተከፍሎ ቢቀርብ እንደሚሻልም እነዚሁ በመስኩ ላይ ምርምርና ጥናት ያካሄዱ ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡ እነዚህ ሦስት ደረጃዎችም ቅድመ ንባብ (pre-reading)፣ በማንበብ ላይ (while-reading) እና ድህረ ንባብ (post-reading) ናቸው፡፡ ከዚህ ቀጥሎም እያንዳንዳቸው አጠር አጠር ባለ መልክ ይቀርባሉ፡፡

#### ሀ. ቅድመ ንባብ /Pre-reading/

ቅድመ ንባብ ተማሪዎች የቀረበውን ጽሑፍ ማንበብ ከመጀመራቸው በፊት የሚከናወኑትን ተግባራት የሚያካትት ሲሆን ሁለት ዐቢይ ዓላማዎች አሉት፡፡ እነሱም ተማሪዎች ምንባቡን የሚያነቡበትን ምክንያት በመግለጽ የማንበብ ፍላጎታቸውን ማነሳሳት እና ስለምንባቡ ይዘት መነሻ ሀሳብ (ፍንጭ) እንዲኖራቸው ማስቻል ናቸው (Getachew 1996፡13)፡፡ በዚህ ቅድመ ንባብ ወቅት ተማሪዎች ምንባቡን የሚያነቡበት ዓላማ ሊገለጽላቸው ይገባል፡፡ ይህም ምንባቡን ምን ያህል ጠለቅ ብለው ማንበብ እንደሚገባቸው ለመወሰን ያግዛቸዋል፡፡

ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ስለምንባቡ ይዘተ ነገርና ምንነት መጠነኛ ግንዛቤና አወንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ የምንባቡ ይዘተ ነገር ምን ሊሆን እንደሚችል ተማሪዎች ስለ ርዕሱ ቀድሞ ካላቸው እውቀት በመነሳት አንዳንድ ሐሳቦች ቢሰነዝሩ ምንባቡን በሚያነቡበት ጊዜ ፍፁም አስቸጋሪ መስሎ አይታያቸውም (Statman 1981፡ 232)፡፡ ይህም ተማሪዎች ጽሑፉን ወደማንበቡ ተግባር ከመሸጋገራቸው በፊት ከርዕሱ በመነሳት ሀሳብ እንዲሰነዝሩ በማነሳሳት፣ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ወዘተ. ይከናወናል፡፡

በቅድመ ንባብ ወቅት ከሚከናወኑት ተግባራት መካከል ሌላው ተማሪዎች በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አዳዲስ ቃላትን ፍችዎች እንዲረዱ ማድረግ እንደሆነ ምሁራን (ለምሳሌ፣ Nuttal: 1982፡ 157) ይጠቁማሉ፡፡ ምንባቡን አንብቦ ለመረዳት እንቅፋት ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱ አዳዲስ ቃላት ፍችዎች ለተማሪዎች በዚህ የቅድመ ንባብ ወቅት ቢቀርቡላቸው ምንባቡን አንብበው ለመረዳት ያግዛቸዋል፡፡

## ለ. <u>በማንበብ ላይ (While-reading)</u>

ይህ ደረጃ ተማሪዎች ጽሑፉን የሚያነቡበትና የንባብ ሂደቱ ዋነኛ አካል ነው፡፡ ይህ ባለ ሦስት ደረጃ የንባብ ትምህርት ተማሪ-መራሽ (Learner – centred) በመሆኑ አብዛኛዎቹ ተግባራት የሚከናወኑት በተማሪዎች ነው፡፡ የመምህሩ ሚናም ለተማሪዎቹ እርዳታ መስጠትና የማንበብ ሂደቱን ማፋጠን ነው (Getachew: 1996፡ 15)፡፡

"ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ምንባቡን ማንበብ ያለባቸው በፀጥታ ነው ወይስ ድምፅን ከፍ በማድረግ ?" የሚለው ጥያቄ በተለያዩ ምሁራን ይነሳል፡፡ ብዙዎቹ ምሁራን (Greenwood: 1981፡81- 82፣ Grellet 1981፡ 10፣ Lewis 1985፡ 111 ፣ Nuttal 1982) እንደሚሉት አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎች ለትምህርት የሚቀርበውን ምንባብ በፀጥታ ቢያነቡት ይመረጣል፡፡ ምሁራኑ እንደሚገልፁት ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሚያነቡበት ጊዜ ምናልባት ድምፁን ከፍ አድርጎ የሚያነበው ተማሪ የአነባበብ ስልት ጥሩ ካልሆነ ሌሎች ተማሪዎችም ልምዱን ሊቀስሙ ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩልም ማንበብ በባህሪው ግላዊ ተግባር ነው ማለት ይቻላል (Molla: 1987፡ 5)፡፡ ተማሪዎችም ንባብን የሚማሩት የተለያዩ ጽሑፎችን አንብበው መረዳት እንዲችሉ እንጅ ሰው ሲያነብ አዳምጠው እንዲገነዘቡ ወይም ለሌላ ሰው እንዲያነቡ አይደለም፡፡ ከዚህ ባሻገርም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሚያነቡበት ጊዜ "አሁን ምን እሳሳት ይሆን?" እያሉ ይጨነቃሉ፡፡ ይህም የሚያነቡትን ምንባብ መረዳታቸውን ሊቀንሰው ይችላል፡፡

ይሁን እንጅ ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ እርባና ቢስ ነው፣ ሙሉ በሙሉም መዘንጋት አለበት ማለት እንዳልሆነ ከላይ የተጠቀሱት ጸሐፍት ይጠቁማሉ፡፡ እንደአስፈላጊነቱ አልፎ አልፎ በተለይም የተማሪውን የአነባበብ ስልት ለመገምገም ሲባል ተግባራዊ ይሆናል፡፡

### ሐ. ድህረ ንባብ /Post-reading/

በዚህ ወቅት ተማሪዎች የአነበቡትን ምንባብ የበለጠ እንዲገነዘቡት የሚያስችሉ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ በዚህ ደረጃ ከሚከናወኑት ተግባራት ውስጥ ስለተነበበው ምንባብ የተለያዩ ጥያቄዎችን ማቅረብና በተማሪዎች እንዲመለሱ ውይይትም እንዲካሄድባቸው ማድረግ ዋነኛው ነው፡፡ የእነዚህ ጥያቄዎች ዋና ትኩረትና ዓላማም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማዳበር ነው (Nuttal፡ 1982፣ Greenwood: 1981፡ 83)፡፡ ስለሆነም ንባብን በማስተማሩ ሂደት አንድ ምንባብ ከተነበበ በኋላ ለተማሪዎች የሚቀርቡት ጥያቄዎች አንብቦ መረዳትን የሚያዳብሩ እንዲሆኑ በጥንቃቄ መዘጋጀት አለባቸው፡፡

የንባብ ትምህርቱን ከዚህ በላይ በቀረቡት ሦስት ደረጃዎች ከፍሎ ማቅረብ ትምህርቱን የበለጠ ውጤታማ ሊያደርገው ይችላል ቢባልም በየክፍለ ጊዜው የሚቀርበው የንባብ ትምህርት ሁልጊዜ በዚህ መልክ ይሰጥ ማለት አስቸጋሪ ነው (Getachew 1996)፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የንባብ ትምህርቱ ከሌሎች ክሂሎች ጋር ተጣምሮ እንጅ ለብቻው ይሰጣል ማለት አይደለም፡፡

## 2.2 አንብቦ የመረዳት ምንነት

አንድን ጽሑፍ አንብቦ መረዳት ሲባል በጽሑፉ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት በተቻለ መጠን መገንዘብ ነው፡፡ ዘርዝር ተደርጎ ሲታይም አንብቦ መረዳት የሚከተሉትን ነጥቦች ያካትታል (Grellet: 1981፡ 4 - 5፣ Greenwood:1981፡ 89፣ Ellis: 1980፡ 141 - 142፣ Heaton: 1975፡ 103)፡፡

ሀ. <u>የቃላትን ፍች መገንዘብ</u>፡- አንባቢው በጽሑፉ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት አውዳዊ ፍች ሊረዳ ይገባዋል፡፡ ይሁን እንጅ የጽሑፉን መልዕክት ለመረዳት የእያንዳንዱን ቃል ፍች ማወቅ የግድ አስፈላጊ ስላልሆነ አንባቢው በጽሑፉ ውስጥ ያሉትን ቃላት ፍችዎች አንድ በአንድ መመርመር አይጠበቅበትም፡፡

ለ. <u>የጽሑፉን ግልጽ መልዕክት (explicitly stated information) መገንዘብ፡-</u> አንባቢው በጽሑፉ ውስጥ በግልጽ የተቀመጠውን መልዕክት እና ይህንን መልዕክት ለማጉላትም ሆነ ለማጠናከር የገቡትን ዝርዝር ሐሳቦች መረዳት አለበት፡፡

ሐ. <u>የጽሑፍን ውስጣዊ (ድብቅ)(implicitly Stated Information) መልዕክት መገንዘብ</u>:- በጽሑፉ ውስጥ በግልጽ የቀረበውን መልዕክት መገንዘብ አንብቦ የመረዳት ዋነኛ አካል ቢሆንም አንባቢው በዚሁ ብቻ ተወስኖ መቅረት የለበትም:: በግልጽ የተቀመጠውን መልዕክት መነሻ በማድረግ፣ በማገናዘብና በመመርመር የሚደረስበትን ውስጣዊ መልዕክትም መረዳት ይበጠቅበታል::

መ. <u>የአያያዦችን ሰዋስዋዊ አገባብና ትርጉም መገንዘብ</u>:- አንድ አንባቢ በሚያነበው ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙትን አያያዦች አገባብ፣ አገልግሎት እና ትርጉም መገንዘብ ይጠበቅበታል:: እነዚህን መገንዘቡ የጽሑፉን መልዕክት ለመረዳት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክትለታል::

ሠ. <u>የጽሑፉን ቅደም ተከተላዊ የሀሳብ ፍሰት መገንዘብ</u>:- አንባቢው በጽሑፉ ውስጥ ያሉትን ዐረፍተ ነገሮች ተናጠላዊ መልዕክት መረዳቱ ብቻ በቂ አይደለም:: ከዚህ ባሻገርም የጽሑፉን ቅደም ተከተላዊ የሀሳብ አገላለጽ፣ አንዱ ዐረፍተ ነገር ከፊተኛውና ከተከታዮቹ ዐረፍተ ነገሮች ጋር ያለውን የሐሳብ ግንኙነት፣ የጽሑፉ የተለያዩ አንቀጾች ያላቸውን የርስ በርስ ግንኙነት ሊረዳ ይገባዋል:: ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ነጥቦች በሙሉ አንብቦ የመረዳት አካላት ናቸው::

## 2.3 <u>አንብቦ የመረዳት ችሎታን መመዘን</u>

በአንድ የተወሰነ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመመዘን የሚያገለግለው ዋና መሳሪያ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና እንደሆነ ምሁራን (Madson: 1983፣ Weir 1990፣ Davey: 1987፣ Stavans: 1993) ይገልጻሉ:: እስከዛሬ ድረስ በእነዚህና በሌሎች ምሁራን አንብቦ የመረዳት ችሎታን በተመለከተ በተካሄዱ አያሌ ጥናቶች ውስጥ በዐቢይ መሣሪያነት ያገለገለው አንብቦ የመረዳት ፈተና ነው:: ስለሆነም አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት በሚዘጋጅ ፈተና ውስጥ የሚካተቱ ዋና ዋና የጥያቄ ዓይነቶች ከዚህ ቀጥሎ ይቀርባሉ::

### 2.3.1 <u>አንብቦ የመረዳት ፈተና ጥያቄ ዓይነቶች</u>

አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት በሚዘጋጁ ፈተናዎች ውስጥ የሚካተቱ የተለያዩ የጥያቄ ዓይነቶች ቢኖሩም ዋና ዋና የሚባሉት የምርጫ ጥያቄዎች እና ነፃ ጥያቄዎች እንደሆኑ ምሁራኑ (Weir: 1990: 43፣ Madson:1983: 76፣ Davey:

1987፡ 179፣ Stavans: 1993፡481) ይገልጻሉ:: እስከዛሬ ድረስ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመመዘን በተካሄዱ ጥናቶች ካገለገሉት ፈተናዎች አብዛኛዎቹ የተዘጋጁት በምርጫ እና ነጻ ጥያቄ ዓይነቶች እንደሆነ ፀሐፍቱ ያስረዳሉ:: ከዚህ ቀጥሎም እነዚህን የፈተና ጥያቄ ዓይነቶች አንድ በአንድ ለመዳሰስ ይሞከራል::

#### 2.3.1.1 <u>የምርጫ ጥያቄዎች (multiple choice questions)</u>

የምርጫ ጥያቄዎች የሚባሉት ተፈታኙ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከሚሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ ያመለክት ዘንድ የሚዘጋጁ ሲሆኑ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሚቀርቡት ምርጫዎችም ሶስት፣ አራት ወይም አምስት ሊሆኑ ይችላሉ (Weir: 1990፡ 43 - 44፣ Williams: 1984፡ 67 - 68፣ Madson: 1983፡ 48 - 49)::

የምርጫ ጥያቄዎች የራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንዳሏቸው ባለሙያዎቹ ይጠቁማሉ:: ከጠንካራና ከደካማ ጎኖቻቸው ውስጥም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

##### ሀ. <u>ጠንካራ ጎን</u>

1. አርሞ ውጤት ከመስጠት አንፃር አስተማማኝ እና ቀላል፣ ጊዜንና ገንዘብንም ቆጣቢ ናቸው::
2. ለሙከራ ያህል በቅድመ ፈተና መልክ በመስጠት የክብደታቸውን ደረጃ፣ የአዘገጃጀት ድክመታቸውንም ለመገምገም አመች ናቸው::
3. በብዙዎቹ ተፈታኞች የተለመዱ በመሆናቸው ከአሰራራቸው አንጻር ግልጽ ናቸው::
4. ጥያቄዎቹን ለመመለስ ምንባቡን አንብቦ ከመረዳት ውጭ ሐሳብን በጽሑፍ ወይም በንግግር የመግለጽ ችሎታን አይጠይቁም::

##### ለ. <u>ደካማ ጎን</u>

1. ተፈታኞቹ የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልሶች ምንባቡን አንብበው ሳይረዱ በግምት ሊያገኟቸው ይችላሉ::
2. ተፈታኞቹ የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልሶች ሊያጧቸው የሚችሉት ምንባቡን ባለመገንዘባቸው ብቻ ሳይሆን ጥያቄዎቹን ባለመረዳታቸውም ሊሆን ይችላል::
3. ለማዘጋጀት ጥንቃቄን ይሻሉ፤ ችሎታን ይጠይቃሉ፤ ጊዜንም ይወስዳሉ::

### 2.3.1.2 ነፃ ጥያቄዎች (open-ended questions)

እነዚህ የጥያቄ ዓይነቶች በተነበበው ጽሑፍ መሠረት በጽሑፍ ወይም በቃል የሚመለሱ ሲሆኑ እንደምርጫ ጥያቄዎች ሁሉ የራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሏቸው፡፡

#### ሀ. ጠንካራ ጎን

1. ተፈታኞቹ ጥያቄዎቹ የተመሠረቱበትን ጽሑፍ አንብበው ካልተረዱ በስተቀር የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልሶች በግምት ሊያገኟቸው አይችሉም፡፡
2. ከአንድ ምንባብ ብዙ ጥያቄዎችን ለማዘጋጀት ያስችላሉ፡፡
3. አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመመዘን የበለጠ አስተማማኝ ናቸው፡፡
4. መጠየቅን፣ መመርመርን፣ ቅደም ተከተላዊ አገላለጽን መረዳትን ወዘተ. በተሻለ ሁኔታ ለመመዘን ያግዛሉ፡፡

#### ለ. ደካማ ጎን

1. አርሞ ውጤት ከመስጠት አንጻር አስተማማኝነታቸው ዝቅተኛ ነው፡፡
2. ከአንብቦ መረዳት አልፎ ሐሳብን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታን ይጠይቃሉ፡፡

የምርጫም ሆነ ነጻ የአንብቦ መረዳት የፈተና ጥያቄዎች የየራሳቸው ጠንካራ ጎኖች ያሏቸውን ያህል ደካማ ጎኖችም እንዳሏቸው ከዚህ በላይ ለመቃኘት ተሞክሯል፡ ከዚህ ቀጥሎም አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት የሚዘጋጅ ፈተና በየትኛው የጥያቄ ዓይነት ላይ ቢመሠረት ይሻላል ? ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ ባለሙያዎች የሰጧቸውን አስተያየቶች መሠረት በማድረግ ለመቃኘት ይሞከራል፡፡

የምርጫ ጥያቄዎች አንድን ምንባብ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመመዘን እንደማያስችሉ Stavans እና Brenda (1993: 493) Anderson እና ሌሎችን (1985)፣ Cohen (1984)፣ Larson (1981) በመጥቀስ ያስገነዝባሉ፡፡ እንደነዚህ ምሁራን አመለካከት የምርጫ ጥያቄዎች ምንባቡን አንብቦ በመረዳቱ ላይ ተጨማሪ ሸክም ይፈጥራሉ፡፡ ጥያቄዎቹን ከነምርጫቸው አንብቦ መረዳቱ እንዲሁም ከተሰጡት ምርጫዎች ውስጥ ትክክለኛ መልሶችን ከአሳሳቾቹ (distractors) መምረጡ ለተፈታኙ አስቸጋሪ ሊሆንበት ይችላል፡፡ ይህም በፈተና ውጤቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ ስለሆነም

አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት ከምርጫ ጥያቄዎች ይልቅ ነጻ ጥያቄዎች ተመራጭነት አላቸው።

ሌሎች ምሁራን (Heining: 1975፡ 13፣ Williams: 1984፡ 67፣ Stavans: 1993፣ 493፣ Tabia: 1996፡ 4) ደግሞ የላይኛውን ሐሳብ ይቃወማሉ። የምርጫ ጥያቄዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን በሚገባ ለመለካት ስለሚያስችሉ ከነጻ ጥያቄዎች የተሻሉ ናቸው። ጥያቄዎቹ በነጻ መልክ ከተዘጋጁ ጥያቄዎቹን ለመመለስ የጽሑፍ ችሎታ አስፈላጊ ነው። በብዙ ሀገሮች በነጻ መልክ በተዘጋጁ አንብቦ የመረዳት የፈተና ጥያቄዎች መመዘኛነት የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ነው ከሚል ማጠቃለያ ላይ ይደረሳል። ይሁን እንጅ ተፈታኞቹ ዝቅተኛ ውጤት ያገኙት የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ ሆኖ ሳይሆን አንብበው የተገነዘቡትን በጽሑፍ አቀናብረው የመግለጽ ችሎታቸው ዝቅተኛ በመሆኑ ሊሆን ይችላል። ስለሆነም አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች አንድን ጽሑፍ አንብቦ ከመገንዘብ አልፎ የመጻፍ ችሎታን የሚጠይቁ ባይሆኑ ይመረጣል።

የምርጫ ጥያቄዎችም አንብቦ ከመረዳት ባሻገር የመጻፍ ችሎታን ስለማይጠይቁ ከነጻ ጥያቄዎች ይሻላሉ። በተለይም በአፍ መፍቻ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመመዘን የምርጫ ጥያቄዎች የበለጠ ተመራጭነት እንዳላቸው በተለያዩ ጥናቶች መረጋገጡን Stavans (1993፡ 493) ይገልጻሉ።

ይህም የዚህን ጥናት አቅራቢ ወደ አንድ ውሳኔ አድርሶታል። የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመመዘን በሚዘጋጅ ፈተና ውስጥ በአንደኛው የጥያቄ ዓይነት ከመወሰን ይልቅ ሁለቱንም የጥያቄ ዓይነቶች ማካተት የጥናቱን ውጤት አስተማማኝ እንደሚያደርገው የጥናቱ አቅራቢ ያምናል። ለዚህም ዋነኛው ምክንያት የአንደኛው የጥያቄ ዓይነት ደካማ ጎን በሌላኛው የጥያቄ ዓይነት ጠንካራ ጎን ስለሚሸፈን (ስለሚካካስ) ነው።

### 2.3.2 <u>የጥሩ አንብቦ መረዳት ፈተና ባህሪያት</u>

የምርጫም ሆኑ ነጻ አንብቦ የመረዳት የፈተና ጥያቄዎች የሚዘጋጁበት ዋነኛ ዓላማ ተፈታኞቹ የቀረበውን ምንባብ አንብበው መረዳት አለመረዳታቸውን ለመመዘን እንደሆነ ቀደም ሲል በ2.3 ስር ተገልጿል። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስም ጥያቄዎቹ ሲዘጋጁና ምንባቦቹ ሲመረጡ ከግንዛቤ የሚወሰዱ ነጥቦች አሉ። ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው (Hughes: 1995፡ 119 - 131)።

ሀ. ከሁሉም በፊት ጥያቄዎቹ በቀረበው ምንባብ ላይ መመስረት አለባቸው፡፡ በሌላ አገላለጽ የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልሶች ለማግኘት የግድ ምንባቡን ማንበብና መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በፈተናው ውስጥ ተፈታኞቹ ጥያቄዎቹ የተመሠረቱበትን ምንባብ ሳያነቡና ሳይረዱ የሚመልሷቸው ጥያቄዎች መካተት የለባቸውም፡፡ ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመመዘን የሚዘጋጁ ፈተናዎች ይህ ባህሪ ይጎድላቸዋል፡፡ ተፈታኞች ጥያቄቹ የተመሰረቱበትን ምንባብ ሳያነቡ ጥያቄዎቹን በትክክል ይመልሷቸዋል፡፡ የዚህም ምክንያቱ ጥያቄዎቹ በምንባቡ ላይ ባለመመስረታቸውና ቅድመ እውቀትን (background knowledge) ስለሚጠይቁ ሊሆን ይችላል፡፡

ለ. በተቻለ መጠን የፈተናው ጥያቄዎች የተጻፉባቸው ቃላት፣ ሐረጋትና ዐረፍተ ነገሮች በቀጥታ ከምንባቡ የተወሰዱ ባይሆን ይመረጣል፡፡ ይህም ተፈታኞቹ ምንባቡን ሳይረዱ ቃላቱን፣ ሀረጋቱንና ዐረፍተ ነገሮችን በማስታወስና ከምንባቡ በማገናዘብ ብቻ የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልሶች እንዳያገኟቸው ለመከላከል ያስችላል፡፡

ሐ. ለፈተናው የሚመረጡት ምንባቦች ለተወሰኑ ተማሪዎች የማያደሉና የተለየ ዕውቀትን የማይጠይቁ ቢሆኑ ይበጃል (Nuttal:1982: 21)፡፡ በመሆኑም አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመመዘን የሚመረጡት ወይም የሚዘጋጁት ምንባቦች ለተፈታኞች እንግዳ (unfamiliar) ማለት ከዚያ በፊት ያላነበቧቸው ቢሆኑ ይመረጣል፡፡ ይሁን እንጅ Hughes (1995) እንደሚሉት የሚመረጡትን ምንባቦች ተፈታኞቹ ከዚያ በፊት ያንብቧቸው ወይም አያንብቧቸው ማወቅ አስቸጋሪ ነው፡፡

### 2.3.3 <u>አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥ</u>

የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመመዘን በዋነኛ መሣሪያነት የሚያገለግለው አንብቦ የመረዳት ፈተና እንደሆነ ቀደም ሲል በ2.3 ውስጥ ተገልጿል፡፡ ተፈታኞቹ በፈተናው ከሚያገኙት ውጤት በመነሳት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ማወቅ ይቻላል (Nuttal: 1982: 37፣ Narayanaswamy 1975: 144፣ Kavale: 1979: 27፣ Fry: 1963)፡፡

Nuttal (1982: 37) እንደሚገልፁት የአንድን ተማሪ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተሰጠው አንብቦ የመረዳት ፈተና ካገኘው ውጤት ማወቅ ይቻላል፡፡ ተፈታኙ በፈተናው ያገኘው ውጤት 70% ከሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታው በቂ ነው ከሚባልበት ደረጃ ላይ

ይገኛል:: Narayanaswamy (1975: 144) እንደሚያስገነዝቡትም በቂ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አለው የሚባል ተማሪ በተለመደው ፍጥነቱ በማንበብ በሚሰራው አንብቦ የመረዳት ፈተና 70% ሊያገኝ ይገባዋል:: ውጤቱ ከ70% በላይ ከሆነም ጥሩ ችሎታ አለው ሊባል ይችላል:: የተፈታኙ ውጤት 50% ወይም ከዚያ በታች ከሆነ ችሎታው በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል::

ተማሪው በተሰጠው ፈተና ያገኘው ውጤት ከ70 - 80 ፐርሰንት ከሆነ በቂ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አለው:: ከ50 - 60 ፐርሰንት ወይም ከ5 - 6 ከአስር ውጤት ካገኘ ችሎታው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል (Fry: 1963: vii)::

Kavale (1979: 27) እንደሚያስገነዝቡትም በአንብቦ መረዳት ፈተናው 90 ወይም ከዚያ በላይ ከመቶ ያገኘ ተማሪ ከፍተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ አለው:: ከ75 - 90 ከመቶ ያገኘ ተማሪ ችሎታም በቂ ከሚባልበት ደረጃ ላይ ይገኛል:: ውጤቱ ከ75% በታች ከሆነ ግን ችሎታው ዝቅተኛ ነው::

አንድ በአፍ መፍቻ ቋንቋው በቂ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አለው የሚባል ተማሪ በሚሰጠው አንብቦ የመረዳት ፈተና ማግኘት ያለበትን ውጤት በተመለከተ Nuttal እና Narayanaswamy በተመሳሳይ ውጤት ይስማማሉ:: Fry እና Kavale የሚስማሙበት ተመሳሳይ ውጤትም ቢሆን ከላይኞቹ ጋር የጎላ ልዩነት የለውም::

ከዚህ በላይ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን በሰነዘሯቸው ሐሳቦች መሠረት ተማሪዎች በሚሰጣቸው አንብቦ የመረዳት ፈተና ከሚያገኙት ውጤት በመነሳት የሚገኙበትን ደረጃ እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል::

ሠንጠረዥ 1:- አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ

| ውጤት | | ደረጃ |
|---|---|---|
| ከ10 | ከ100 | |
| 10 - 9 | 100 - 90 | ከፍተኛ |
| 8 - 7 | 80 - 70 | መካከለኛ /በቂ/ |
| 6 - 5 | 60 - 50 | ዝቅተኛ |
| ከ4 በታች | ከ40 በታች | በጣም ዝቅተኛ |

# ምዕራፍ ሦስት

## የአጠናን ዘዴ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በጥናቱ የተካተቱት የናሙና ትምህርት ቤቶች፣ ተጠኝ ተማሪዎች እና መጠይቅ በመሙላት የተሳተፉ መምህራን የአመራረጥ ስልት ይጠቆማል፡፡ የመረጃ መሰባሰቢያ ዘዴዎችም ይመላከታሉ፡፡

### 3.1 የናሙና አመራረጥ

#### 3.1.1 የትምህርት ቤቶች አመራረጥ

በዚህ ጥናት ውስጥ የታቀፉት አራት ትምህርት ቤቶች የተመረጡት በተራ እጣ የናሙና አመራረጥ (simple random sampling) ስልት ነው፡፡ ይህ የናሙና አወሳሰድ ስልት የተመረጠበት ምክንያትም በአዲስ አበባ ውስጥ ለሚገኙ የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እኩል የመመረጥ ዕድል ስለሚሰጥ ነው፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙት የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከማስተማሪያ መሣሪያዎች ዓይነት፣ ከክፍል ጊዜ ምደባ ወዘተ. አንፃር ተመሳሳይ በመሆናቸው ሁሉም እኩል የመመረጥ ዕድል እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡

የአመራረጥ ሂደቱም የሚከተለውን ይመስላል፡፡ በመጀመሪያ በአዲስ አበባ የሚገኙት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ስሞች ተመጣጣኝ መጠን ባላቸው ወረቀቶች ላይ ተጻፉ፡፡ ወረቀቶችም በተመሳሳይ ስልትና መጠን ከተጠቀለሉ በኋላ በአንድ ላይ ተቀላቀሉ፡፡ ከዚያም አራቱ የተጠቀለሉ ወረቀቶች ብቻ በየተራ በእጣ እንዲወጡ ተደረገ፡፡ በእጣ በወጡት አራት ወረቀቶች ላይ የተጻፉት ትምህርት ቤቶችም በናሙናነት ተወስደዋል፡፡ እነዚህ ትምህርት ቤቶችም ከፍተኛ 23 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ከፍተኛ 12 አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ኮልፌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ወንድይራድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው፡፡

#### 3.1.2 የተማሪዎች አመራረጥ

በዚህ ጥናት ውስጥ የታቀፉት የናሙና ትምህርት ቤቶች ተለይተው ከታወቁ በኋላ የሚቀጥለው ተግባር ተጠኝ ተማሪዎችን መምረጥ ነበር፡፡ በናሙናነት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በየምድቦቹ የተመደቡት

ከችሎታቸው አንፃር አለመሆኑ ከየትምህርት ቤቶቹ በተገኘው መረጃ በመረጋገጡ ተጠኝ ተማሪዎቹን ከሁሉም ምድቦች መምረጥ የግድ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም። ስለሆነም ተጠኝ ተማሪዎች በሚከተለው መንገድ ከተወሰኑ ምድቦች ተመርጠዋል።

1. በእያንዳንዱ በናሙናነት የተመረጠ ትምህርት ቤት ውስጥ በ11ኛ ክፍል የሚገኙ ምድቦች ብዛት ተለይቶ ከታወቀ በኋላ ከጠቅላላው የምድቦች ብዛት ውስጥ ሃያ አምስት ከመቶው በተራ እጣ የናሙና አወሳሰድ (simple random sampling) ስልት ተመረጡ። ለዚህም በመጀመሪያ በእያንዳንዱ በናሙናነት የተመረጠ ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚገኙት የ11ኛ ክፍል ምድቦች በትምህርት ቤቱ የተሰጡት መለያ ቁጥሮች ወይም የእንግሊዝኛ ፊደላት ለየብቻ ተመጣጣኝ መጠን ባላቸው ወረቀቶች ላይ ተጻፉ። ከዚያም ሃያ አምስት በመቶ የሚሆኑት በእጣ እንዲወጡ ተደረገ። ለምሳሌ በጥናቱ ውስጥ የተካተተ ትምህርት ቤት የ11ኛ ክፍል ምድቦች ብዛት አስራ ሁለት ቢሆን በናሙናነት የሚመረጡት ምድቦች ብዛት ሶስት (12 x 25/100 = 3) ይሆናል።

2. በናሙናነት ከተመረጠ እያንዳንዱ ምድብ ከሚገኙት ተማሪዎች ውስጥ ሃያ አምስት ከመቶ የሚሆኑት በማይለወጥ ሥርዓታዊ የናሙና አመራረጥ ስልት (linear systematic sampling) ተመረጡ። ይህም እንደሚከተለው ተከናውኗል። በመጀመሪያ በተመረጡት ምድቦች ውስጥ የሚገኙት ተማሪዎች የስም ዝርዝር ከክፍል ኃላፊ መምህራን የስም መቆጣጠሪያ ላይ ተወሰደ። በስም መቆጣጠሪያውም ሃያ አምስት ከመቶ የሚሆኑት ተማሪዎች ብዛት ታወቀ። ለምሳሌ በምድቡ ውስጥ የሚማሩት ተማሪዎች 64 ቢሆኑ ከዚህ ምድብ የሚመረጡት ተማሪዎች አስራ ስድስት (64 x 25/100 = 16) ይሆናሉ። እነዚህ አስራ ስድስት ተማሪዎችም በስም መቆጣጠሪያ ዝርዝሩ ላይ አራት፣ አራት በመዝለል (64 ÷ 16 = 4) የሚገኙት ይሆናሉ። በዚህም መሠረት በስም መቆጣጠሪያው ላይ በተራ ቁጥር 1፣ 5፣ 9፣ 13፣ 17፣. . .63 የተመዘገቡት ተማሪዎች ለጥናቱ ይመረጣሉ ማለት ነው።

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ዘዴዎች ለጥናቱ የተመረጡት ትምህርት ቤቶች ምድቦችና የተማሪዎች ብዛት በሚከተለው ሠንጠረዥ ተመላክቷል።

ሠንጠረዥ 2፡- በናሙናነት የተመረጡ ትምህርት ቤቶች፣ ምድቦችና ተማሪዎች ብዛት

| ተራ ቁ. | ትምህርት ቤት | ጠቅላላ የምድቦች ብዛት | በናሙናነት የተመረጡ ምድቦች ብዛት | በተመረጡ ምድ ቦች ውስጥ የሚ ማሩ ተማሪዎች ብዛት | በናሙናነት የተወሰዱ ተማሪዎች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ወ | ሴ | ድምር | % |
| 1 | ከፍተኛ 23 | 12 | 3 | 271 | 38 | 30 | 68 | 25% |
| 2 | ከፍተኛ 12 | 11 | 3 | 195 | 30 | 21 | 51 | 25% |
| 3 | ኮልፌ | 11 | 3 | 218 | 31 | 24 | 55 | 25% |
| 4 | ወንድይራድ | 10 | 3 | 204 | 24 | 27 | 51 | 25% |
| ድ ም ር. . . . . . . . | | 44 | 12 | 888 | 123 | 102 | 225 | 100% |

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ መገንዘብ እንደሚቻለው በጥናቱ ከታቀፉት አራት ትምህርት ቤቶች የተመረጡት ተማሪዎች 225 ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ 123ቱ ወንዶች 102ቱ ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡

### 3.1.3 የመምህራን አመራረጥ

ለዚህ ጥናት በመረጃ ማሰባሰቢያነት የተዘጋጀውን የጽሑፍ መጠይቅ (አባሪ 1ን ይመለከቷል) የሞሉትን መምህራን በአዲስ አበባ ከሚገኙ የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሙሉ ለመምረጥ ከአቅም በላይ በመሆኑ የናሙና መምህራኑ ከተወሰኑ ትምህርት ቤቶች ብቻ ተመርጠዋል፡፡ በዚህም መሠረት ለጥናቱ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች 11ኛ ክፍሎች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ መምህራን በሙሉ የተዘጋጀውን መጠይቅ እንዲሞሉ ታድሏቸዋል፡፡

ሠንጠረዥ 3፡- የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉ መምህራን

| ተራ ቁጥር | ትምህርት ቤት | የ11ኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን ብዛት | መጠይቁ የታደላቸው መምህራን ብዛት | መጠይቁን ሞልተው የመለሱት ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ 23 | 4 | 4 | 4 |
| 2 | ከፍተኛ 12 | 4 | 4 | 4 |
| 3 | ኮልፌ | 4 | 4 | 4 |
| 4 | ወንድይራድ | 3 | 3 | 3 |
| ድ ም ር . . . . | | 15 | 15 | 15 |

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው መጠይቁ ለአስራ አምስት መምህራን የታደለ ሲሆን ሁሉም የታደላቸውን መጠይቅ ሞልተው መልሰዋል፡፡

## 3.2 የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች

ለዚህ ጥናት መረጃዎችን ለማሰባሰብ በዋነኛ መሣሪያነት ያገለገሉት ዘዴዎች ሶስት ናቸው፡፡ እነሱም 1ኛ/ ለመምህራን የተሰራጨ የጽሑፍ መጠይቅ፣ 2ኛ/ የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ምልከታ፣ 3ኛ/ ለተማሪዎች የተሰጡ አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች ናቸው፡፡ በመምህራን ከተሞላ የጽሑፍ መጠይቅ፣ ከክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ምልከታ እና ለተማሪዎች ከተሰጡ አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ከዚህ ቀጥሎም እያንዳንዱን የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ለማብራራት ይሞከራል፡፡

### 3.2.1 ለመምህራን የተሰራጨ የጽሑፍ መጠይቅ

ለጥናቱ መረጃ ለማሰባሰብ ያገለገለው የጽሑፍ መጠይቅ በክለሳ ድርሳናቱ ውስጥ የተጠቀሱትን ነጥቦች መሠረት በማደረግ በአጥኚው ተዘጋጅቶ በባለሙያዎች ሀሳብና አስተያየት ከተሰጠበት በኋላ በናሙናነት የተመረጡት መምህራን እንዲሞሉት ተደርጓል፡፡

መጠይቁ ሶስት ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ክፍል አጠቃላይ መረጃን (የመምህራንን ፆታና የትምህርት ደረጃ፣ የሰለጠኑበትን የትምህርት ዓይነት፣ ወዘተ.) የሚመለከቱ ጥያቄዎችን አካቷል፡፡ መምህራኑ መልሶቻቸውን የሚጽፉባቸው ባዶ ቦታዎችም በየጥያቄዎቹ አንፃር ተሰጥተዋል፡፡

የመጠይቁ የሁለተኛውና የሶስተኛው ክፍሎች ደግሞ በክፍል ውስጥ የሚካሄደውን የንባብ ልምድ፣ የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ የንባብ ተሳትፎ፣ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ወዘተ. የሚመለከቱ ጥያቄዎችን አካተዋል፡፡ በክፍል ሁለት ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ ጥያቄ የየራሱ ምርጫዎች የተሰጡት ሲሆን መምህራኑም ከተሰጡት ምርጫዎች ውስጥ የሚስማሙበትን እንዲመርጡ ተጠይቀዋል፡፡ በክፍል ሶስት ውስጥ ለተካተቱት ጥያቄዎችና ሐሳቦች ደግሞ አንድ ዓይነት የሆኑ አምስት አምስት መመዘኛዎች ተሰጥተዋል፡፡ እነዚህ መመዘኛዎችም በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ የሚሉ ናቸው፡፡ መምህራኑም ለእያንዳንዱ ጥያቄ ወይም ሐሳብ የሚስማሙበትን መመዘኛ መርጠው እንዲያመለክቱ ተገልጾላቸዋል፡፡ የመጠይቁ አራተኛ ክፍል መምህራኑ መልሶቻቸውንና አስተያየቶቻቸውን በነጻ የሚገልፁባቸውን ጥያቄዎች ይዟል፡፡

መጠይቁ ዓላማው በግልጽ ከተቀመጠና በእያንዳንዱ ክፍል ሥር የሚገኙ ጥያቄዎችን አመላለስ በተመለከተም ግልጽ መመሪያዎች ከተጻፉበት በኋላ መምህራኑ እንዲሞሉት ተደርጓል፡፡

### 3.2.2 የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ምልከታ

የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከሚወሰንባቸው ነጥቦች ውስጥ በክፍል ውስጥ የሚካሄደው የንባብ ትምህርት ዋነኛው ነው (Getachew: 1996)፡፡ በመሆኑም በ11ኛ ክፍል ውስጥ የንባብ ልምምዱ እንዴት እንደሚካሄድ መረጃ ለማግኘት ሲባል ምልከታዎች ተካሂደዋል፡፡

ምልከታዎቹን ለማካሄድም ፈቃደኛ መምራንን ማግኘትና የንባብ ልምምድ የሚካሄድባቸውን ክፍለ ጊዜያት ማወቅ አስፈላጊ ነበር፡፡ ስለሆነም በየትምህርት ቤቶቹ የ11ኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን መካከል ሙሉ ፈቃደኛ የሆኑና የንባብ ልምምድ የሚካሄድባቸውን ክፍለ ጊዜያት ለአጥኚው ያሳወቁ ሁለት ሁለት መምህራን ተመርጠዋል፡፡ ለመምህራኑ የምልከታው ዓላማ በሚገባ የተገለጸላቸው ሲሆን በምልከታው ወቅትም ሁልጊዜ የሚገለገሉበትን ስልት እንዲከተሉ ማሳሰቢያ ተሰጥቷቸዋል፡፡

ሁሉም ምልከታዎች አንድ አንድ ለትምህርት የቀረበ ምንባብ ተጀምሮ እስከሚፈፀምበትና አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች እስከሚመለሱበት ድረስ ያለውን የጊዜ ገደብ እንዲያጠቃልሉ ተደርጓል፡፡ ይህም ከአንድ እስከ ሁለት የአርባ ደቂቃ ክፍለ ጊዜያትን ፈጅቷል፡፡

ምልከታዎቹ የተካሄዱት በክለሳ ድርሳናቱ ውስጥ በቋንቋ ትምህርት ባለሙያዎች ስለንባብ ትምህርት አሰጣጥ የተገለፀውን በመመርኮዝ በተዘጋጀ የምልከታ ዝርዝር መሣሪያነት ነው (አባሪ 2ን ያገናዝቧል)፡፡ የምልከታ ዝርዝሩ በክፍሉ ውስጥ የንባብ ትምህርት ወቅት ተግባራዊ ይሆናሉ ተብለው የታሰቡ ዝርዝር ነጥቦችን ያካተተ ነው (Gage: 1963፡ 298 - 299)፡፡ ምልከታውን የሚያካሂዱት ባለሙያዎች መብዛት በመምህሩም ሆነ በተማሪዎች ላይ የመደናገር ስሜት ስለሚፈጥር ምልከታው በአንድ ባለሙያ ብቻ ቢካሄድ እንደሚሻል በተጠቆመው መሠረት (Gage: 1963፡ 306) ይህን ሁኔታ ከግንዛቤ በማስገባት በዚህ ጥናት ውስጥ ምልከታዎቹ የተካሄዱት በአንድ ባለሙያ (በአጥኚው) ብቻ ነው፡፡ ምልከታዎቹ በሚካሄዱበት ጊዜ በምልከታ ዝርዝሩ ውስጥ የሰፈሩት ነጥቦች (ሐሳቦች) በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ከሆኑ በየአንጻሩ በተሰጡ ቦታዎች የ " √ " ምልክት፣ ካልሆኑ ደግሞ

የ"× " ምልክት ተደርጓል:: ምልክታዎቹ በዚህ መልክ ተካሂደው መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ ተተንትነው ቀርበዋል::

### 3.2.3 አንብቦ የመረዳት ፈተና

#### 3.2.3.1 አዘገጃጀት

በአንድ የተወሰነ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመመዘን የሚያስችለው ዋነኛ ዘዴ የአንብቦ መረዳት ፈተና አዘጋጅቶ መስጠት እንደሆነ ምሁራንን (Weir : 1990፣ Madson: 1983፣ Davey: 1987 Stavans: 1993) በመጥቀስ ቀደም ሲል በክለሳ ድርሳናቱ ውስጥ ተገልጿል::

በዚህ ጥናት ውስጥ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመለካት ሲባል ሁለት አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች (አባሪ 2 ሀ እና ለን ይመለከቷል) በአጥኚው ተዘጋጅተው ተጠኚዎቹ እንዲፈተኗቸው ተደርጓል:: ፈተናዎቹ ሁለት የሆኑበት ምክንያትም በአንድ ፈተና ላይ ብቻ ከመመስረት ይልቅ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ፈተናዎችን መስጠት የጥናቱን ውጤት የበለጠ አስተማማኝ ስለሚያደርገው ነው (Harris: 1965፣ Madson: 1983)::

አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመመዘን ከሚያገለግሉት የጥያቄ ዓይነቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የምርጫ እና ነጻ የሚባሉት እንደሆኑ ምሁራንን (Weir: 1990፣ Madson: 1983፣ Stavans: 1993) በዋቢነት በመጥቀስ በክለሳ ድርሳናቱ ውስጥ ተገልጿል:: ለዚህ ጥናት መረጃ ማሰባሰቢያነት በተዘጋጁት ሁለት ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት የጥያቄ ዓይነቶችም የምርጫ እና ነጻ ጥያቄዎች ናቸው::

በእያንዳንዱ ፈተና ውስጥ አስር አስር ጥያቄዎች ተካተዋል:: በሁለቱም ፈተናዎች ውስጥ የሚገኙት የምርጫ እና ነጻ ጥያቄዎች ብዛትም እኩል ነው:: የምርጫ ጥያቄዎች መልሶቻቸው በግምታዊ አሰራርና ለመልሶችም ፍንጭ በሚሰጡ የአዘገጃጀት ድክመቶች እንዳይገኙ ጥንቃቄ ለማድረግ ተሞክሯል:: ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት ምርጫዎች ውስጥ አሳሳቾችን ከትክክለኛ መልሶች ጋር ለማመሳሰልና እንዲያሳስቱ ለማድረግም ተሞክሯል::

ለሁለቱ ፈተናዎች የተመረጡት ምንባቦች በተፈታኞቹ ጠቅላላና የቀድሞ ዕውቀት ላይ እንዳይመሠረቱ፣ የተለየ ዕውቀትንም እንዳይጠይቁ ጥረት ተደርጓል (Marks: እና

Nou: 1967፣ 336፣ Hughes: 1995)። በአንብቦ መረዳት ፈተና ውስጥ የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልሶች ለማግኘት ጥያቄዎቹ የተመሠረቱበትን ምንባብ ማንበብና መረዳት የግድ በመሆኑ ተፈታኞቹ ምንባቦቹን ሳያነቡና ሳይረዱ ቀድሞ ባላቸው ዕውቀት ወይም ያዘገጃጀት ድክመት የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልሶች እንዳያገኟቸው ሲባል የተቻለው ሁሉ ጥንቃቄ ተደርጓል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትንና የመሳሰሉትን ነጥቦች ሁሉ ከግንዛቤ በማስገባት የተማሪዎችን ደረጃ ይመጥናሉ፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታንም ይመዝናሉ ተብሎ የታመነባቸው ፈተናዎች በአጥኚው ከተዘጋጁ በኋላ በሁለት የቋንቋ እና በሌሎች ሁለት የሥነ አእምሮ (Psychology) ምሁራን ተገምግመውና መሻሻል ተደርጎባቸው እንደገና ተዘጋጅተዋል። እንደገና የተዘጋጁት ፈተናዎችም በባለሙያዎቹ ተገምግመው ተገቢነት (Validity) እንዳላቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል።

የፈተናዎችን አስተማማኝነት (reliability) ለማረጋገጥ ሲባልም ፈተናዎች ለዋናው ጥናት ከመዋላቸው በፊት አርባ የሚሆኑ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲፈተኗቸው ከተደረገና ከታረሙ በኋላ አስተማማኝነታቸው በ'Crombach Alpha' የአስተማማኝነት መለኪያ ቀመር ተሰልቷል። በስሌቱ የተገኘው የአስተማማኝነት ውጤትም 0.82 ሆኗል (አባሪ 4 ሀን ያገናዝቧል)። ይህ ውጤትም የሁለቱን ፈተናዎች አስተማማኝነት ያመላክታል። የሁለቱ ፈተናዎች ውጤት ዝምድናም (Correlation) በ'Pearson product moment correlation' ተሰልቶ ውጤቱ 0.83 ሆኗል (አባሪ 4 ለን ይመላከቷ)። ይህም እያንዳንዱ ተማሪ በእያንዳንዱ ፈተና ተቀራራቢነት ያለው ውጤት ማግኘቱን ያሳያል። ይህ ደግሞ የፈተናዎቹ የክብደት ደረጃ ተመጣጣኝ መሆኑን ያመላክታል።

### 3.2.3.2 አሰጣጥና አስተራረም

ፈተናዎቹ ከዚህ በላይ በተገለፀው መልክ ተዘጋጅተው፣ አሰራራቸውን በተመለከተም ግልጽ መመሪያዎች ተጽፈውባቸው ለጥናቱ የተመረጡት ተማሪዎች እንዲሰሯቸው ተደርጓል። ፈተናዎቹ ለተጠኚዎቹ የተሰጡት በሁለት ተከታታይ ሳምንታት ውስጥ ነው። በመጀመሪያው ሳምንት ፈተና አንድ የተሰጠ ሲሆን፣ በተከታዩ ሳምንት ደግሞ ፈተና ሁለት ተሰጥቷል።

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ውጤት ትንተና እና ገለጻ

### 4.1 የመረጃ ውጤት ትንተና

በዚህ ንኡስ ክፍል ስር በተለያዩ የመረጃ ማሰባሰቢያ መንገዶች የተገኙ መረጃዎች እየተተነተኑ ይቀርባሉ።

#### 4.1.1 ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ለዚህ ጥናት አንዱ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ለመምህራን የተሰራጨ የጽሑፍ መጠይቅ እንደሆነ በ3.2.1 ተገልጿል። ከዚህ በታች በመጠይቁ የተገኙ መረጃዎች ይተነተናሉ።

ሀ. በክፍል አንድ ከቀረቡ ጥያቄዎች የተገኙ መረጃዎች

ሠንጠረዥ 4፡ መጠይቁን ሞልተው የመለሱ መምህራን በፆታ

| ተ.ቁ. | ፆታ | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | ወንድ | 11 | 73.3 |
| 2 | ሴት | 4 | 26.7 |
| | ድምር . . . . . . . | 15 | 100 |

ሠንጠረዥ 5፡ መጠይቁን ሞልተው የመለሱ መምህራን በትምህርት ደረጃ

| ተ.ቁ. | የትምህርት ደረጃ | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | ዲፕሎማ | 4 | 26.7 |
| 2 | ቢ.ኤ. ዲግሪ | 10 | 66.7 |
| 3 | ኤም.ኤ. ዲግሪ | 1 | 6.7 |
| ድምር . . . . . . . . . | | 15 | 100 |

ሠንጠረዥ 6፡ መጠይቁን ሞልተው የመለሱ መምህራን በሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት

| ተ.ቁ. | የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | አማርኛ | 15 | 100 |
| 2 | ሌላ | - | - |
| ድምር | | 15 | 100 |

ሠንጠረዥ 7፡ መጠይቁን ሞልተው የመለሱ መምህራን በአገልግሎት ዘመን

| ተ.ቁ. | የአገልግሎት ዘመን | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | ከ 1 - 5 ዓመት | 2 | 13.3 |
| 2 | ከ 6 - 10 " | - | - |
| 3 | ከ11 - 15 " | 4 | 26.7 |
| 4 | ከ16 - 20 " | 6 | 40.0 |
| 5 | ከ21 - 25 " | 2 | 13.3 |
| 6 | ከ26 - 30 " | 1 | 6.7 |
| ድምር . . . . . . . . | | 15 | 100 |

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ሠንጠረዦች (4 - 7) መረዳት እንደሚቻለው መጠይቁን ሞልተው ከመለሱት 15 መምህራን ውስጥ አስራ አንዱ (73.3%) ወንዶች ሲሆኑ አራቱ (26.7%) ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ በትምህርት ደረጃቸው አንፃር ዲፕሎማ፣ ቢ.ኤ. ዲግሪና ኤም.ኤ. ዲግሪ ያላቸው መምህራን ብዛት በዚሁ ቅደም ተከተል መሠረት 4 (26.7%)፣ 10(66.7%) እና 1(6.7%) ሲሆን ሁሉም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት የአማርኛ ቋንቋ ነው፡፡ ቋንቋውን በማስተማር ካላቸው ልምድ አኳያ ከ1-5፣ ከ11-15፣ ከ16-20፣ ከ21 - 25 ዓመታት እና ከ26 ዓመት በላይ ያገለገሉት መምህራን ብዛት እንደ ቅደም ተከተሉ 2(13.3%)፣ 4(26.7%)፣ 6(40%)፣ 2 (13.3%) እና 1(6.7%) ነው፡፡

ከዚህ በላይ እንደተመለከተው የመምህራኑ የትምህርት ደረጃ፣ የሰለጠኑበት የትምህት ዓይነት፣ የአገልግሎት ዘመን ወዘተ. የሚጠቁሙት መምህራኑ ለጥናቱ ተገቢና ጠቃሚ መረጃዎችን ሊሰጡ እንደሚችሉ ነው፡፡

## ለ. በክፍል ሁለት ከቀረቡ ጥያቄዎች የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ሠንጠረዥ 8፡- የክፍሉ ውስጥ የአማርኛ ትምህርት እና የመማሪያ መጽሐፍ ይበልጥ የሚያተኩሩበትን በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች

| የጥያቄው ተ.ቁ. | ጥያቄ | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | በክፍል ውስጥ የሚቀርበው የአማርኛ ትምህርት ይበልጥ የሚያተኩረው በየትኛው ክሂል ላይ ነው ? | | |
| | ሀ. በማዳመጥ | 1 | 6.7 |
| | ለ. በመናገር | 2 | 13.3 |
| | ሐ. በማንበብ | 8 | 53.3 |
| | መ. በመጻፍ | 4 | 26.7 |
| 2 | በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይበል የሚያጎለብተው የትኛውን ነው ? | | |
| | ሀ. አዳምጦ የመረዳት ችሎታን | 1 | 6.7 |
| | ለ. ሐሳብን በንግግር የመግለጽ ችሎታን | 3 | 20.0 |
| | ሐ. አንብቦ የመረዳት ችሎታን | 6 | 40.0 |
| | መ. ሐሳብን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታን | 5 | 33.3 |
| 4 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት መልመጃዎች ይበልጥ የሚያተኩሩት በየትኛው ላይ ነው ? | | |
| | ሀ. አዳምጦ በመረዳት | 1 | 6.7 |
| | ለ. ሐሳብን በንግግር በመግለጽ | 2 | 13.3 |
| | ሐ. አንብቦ በመረዳት | 7 | 46.7 |
| | መ. ሐሳብን በጽሑፍ በመግለጽ | 5 | 33.3 |

ከዚህ በላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከቱት ጥያቄዎች የክፍሉ ውስጥ የአማርኛ ትምህርት እና የመማሪያ መጽሐፍ ይበልጥ ስለሚያተኩሩበትና ስለሚያጎለብቱት የክሂል ዘርፍ መረጃ ለማግኘት የቀረቡ ናቸው፡፡ በክፍል ውስጥ የሚቀርበው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይበልጥ የሚያተኩረው በማንበብ ክሂል ላይ እንደሆነ ከመጠይቁ መላሾች አብዛኞቹ (53.3%) ገልፀዋል፡፡

የ2ኛው ጥያቄ ትምህርቱ ይበልጥ የሚያጎለብተውን በተመለከተ የቀረበ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄም ቢሆን በብዙዎቹ /40%/ የተመረጠው "አንብቦ የመረዳት ችሎታን" የሚለው ነው፡፡ በ4ኛው ተራ ቁጥር ላይ ለቀረበው ጥያቄ በብዛት የተሰጠው መልስ "አንብቦ በመረዳት ላይ" የሚል ነው፡፡ ይህን መልስ የሰጡትም 46.7% ናቸው፡፡

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው፣ በክፍል ውስጥ የሚቀርበው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይበልጥ የሚያተኩረው በማንበብ ክሂል ላይ፣ ይበልጥ የሚያጎለብተውም አንብቦ የመረዳት ችሎታን ሲሆን፣ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት መልመጃዎችም ይበልጥ የሚያተኩሩት በአንብቦ መረዳት ላይ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 9፡- መልመጃዎችን ለተማሪዎች ስለመስጠትና ስለማረም የተገኙ መረጃዎች

| የጥያቄው ተ.ቁ. | ጥያቄ | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 3 | ለሚያስተምሯቸው ተማሪዎች መልመጃዎችን ምን ያህል ይሰጣሉ ? | | |
| | ሀ. ሁልጊዜ እሰጣለሁ | 3 | 20.0 |
| | ለ. አብዛኛውን ጊዜ እሰጣለሁ | 10 | 66.7 |
| | ሐ. አልፎ አልፎ እሰጣለሁ | 2 | 13.3 |
| 5 | ለተማሪዎች የሚሰጧቸውን መልመጃዎች ምን ያህል ተከታትለው ያርማሉ ? | | |
| | ሀ. ሁልጊዜ አርማለሁ | 4 | 26.7 |
| | ለ. አብዛኛውን ጊዜ አርማለሁ | 8 | 53.3 |
| | ሐ. አልፎ አልፎ አርማለሁ | 3 | 20.0 |
| 6 | ከሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ውስጥ በየጊዜው የሚሰጧቸውን መልመጃዎች የሚሰሩ ምን ያህሉ ናቸው? | | |
| | ሀ. ሁሉም ይሰራሉ | 1 | 6.7 |
| | ለ. አብዛኞቹ ይሰራሉ | 5 | 33.3 |
| | ሐ. ጥቂቶቹ ይሰራሉ | 9 | 60.0 |

ከዚህ በላይ የቀረበው ሠንጠረዥ የአማርኛ መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው መልመጃዎችን ከመስጠትና ከማረም አኳያ ያላቸውን ልምድ የሚመለከቱ ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ መጠይቁን ሞልተው ከመለሱት መምህራን ውስጥ አብዛኞቹ (86.6%) ለተማሪዎቻቸው መልመጃዎችን ሁልጊዜ እና አብዛኛውን ጊዜ እንደሚሰጡ ገልፀዋል፡፡ ለተማሪዎቻቸው የሚሰጧቸውን መልመጃዎች ተከታትለው ማረማቸውን በተመለከተም 80% "ሁልጊዜ አርማለሁ" እና "አብዛኛውን ጊዜ አርማለሁ" በማለት መልሰዋል፡፡

6ኛው ጥያቄ የሚሰጧቸውን መልመጃዎች የሚሰሩት ተማሪዎች ምን ያህሉ እንደሆኑ ይጠይቃል፡፡ መጠይቁን ሞልተው ከመለሱት መምህራን ውስጥ 40% "ሁሉም

ይሰራሉ" እና "አብዛኞቹ ይሰራሉ" የሚል መልስ ሲሰጡ 60% ደግሞ ጥቂቶች ይሰራሉ በማለት መልሰዋል፡፡

ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ከመጠይቁ በተገኘው መረጃ መሠረት መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው መልመጃዎችን ይሰጣሉ፤ የሰጧቸውን መልመጃዎችም ተከታትለው ያርማሉ፡፡ ይሁን እንጅ የሚሰጧቸውን መልመጃዎች የሚሰሩት ተማሪዎች ቁጥር አነስተኛ እንደሆነ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ይህም በተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ አይቀርም፡፡

ሠንጠረዥ 10፡- የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ የንባብ ልምምድ በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች

| የጥያቄው ተ.ቁ. | ጥያቄ | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 7 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች እንዲያነቡ የሚደረገው፣ | | |
| | ሀ. ሁልጊዜ ነው | 2 | 13.3 |
| | ለ. አብዛኛውን ጊዜ ነው | 5 | 33.3 |
| | ሐ. አልፎ አልፎ ነው | 8 | 53.3 |
| | መ. በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ አይደረግም | - | - |
| 8 | ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ካሉት ምንባቦች ውጭ ሌላ ተጨማሪ ምንባቦችን የሚያነቡት፣ | | |
| | ሀ. ሁልጊዜ ነው | - | - |
| | ለ. አብዛኛውን ጊዜ ነው | 2 | 13.3 |
| | ሐ. አልፎ አልፎ ነው | 4 | 26.7 |
| | መ. ሌሎች ተጨማሪ ምንባቦችን አያነቡም | 9 | 60.0 |
| 9 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች በሚያነቡበት ጊዜ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በየተራ እንዲያነቡ የሚደረገው | | |
| | ሀ. ሁልጊዜ ነው | 4 | 26.7 |
| | ለ. አብዛኛውን ጊዜ ነው | 8 | 53.3 |
| | ሐ አልፎ አልፎ ነው | 3 | 20.0 |
| | መ. ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በየተራ እንዲያነቡ አይደረግም | - | - |
| 10 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች በየተራ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው የሚያነቡ ከሆነ ሲሳሳቱ ምን እርምጃ ይወስዳሉ? | | |
| | ሀ. አስተካክለው እስኪያነቡት ድረስ የተሳሳቱን እንዲደግሙ አደርጋለሁ | 8 | 53.3 |
| | ለ. የንባብ ሂደቱን በማቋረጥ ስህተቱን እራሴ አስተካክየ አነባለሁ | 6 | 40.0 |
| | ሐ. መሳሳታቸውን ያላወቅሁ በመምሰል ንባባቸውን | 1 | 6.7 |

| የጥያቄው ተ.ቁ. | ጥያቄ | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 11 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች በሚያነቡበት ጊዜ ድምፃቸውን ሳያሰሙ (በዝምታ) እንዲያነቡ የሚደረገው፣ | | |
| | ሀ. ሁልጊዜ ነው | 1 | 6.7 |
| | ለ. አብዛኛውን ጊዜ ነው | 4 | 26.7 |
| | ሐ. አልፎ አልፎ ነው | 7 | 46.7 |
| | መ. ድምፃቸውን ሳያሰሙ (በዝምታ) እንዲያነቡ አይደረግም | 3 | 20.0 |

በክፍል ውስጥ የሚካሄደው የንባብ ልምምድና የተማሪዎች ተሳትፎ ምን እንደሚመስል መረጃ ለማግኘት ሲባል በሠንጠረዥ 10 ውስጥ ያሉት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በጥያቄ 7 እንደተመለከተው ተማሪዎች ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ የሚደረገው አልፎ አልፎ እንደሆነ የገለፁት መምህራን 53.3% ናቸው፡፡ ይህም ሌሎችን መልሶች ከሰጡት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ነው፡፡ በተራ ቁጥር 8 ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ካሉት ምንባቦች ውጭ ሌሎች ተጨማሪ ምንባቦችን እንዲያነቡ የሚደረገው ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ሲባል ለቀረበው ጥያቄ ብዙዎቹ (60%) የሰጡት መልስ "ሌሎች ተጨማሪ ምንባቦችን አያነቡም" የሚል ነው፡፡

9ኛው ጥያቄ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሁልጊዜም ይሁን አብዛኛውን ጊዜ ወይም አልፎ አልፎ በሚያነቡበት ጊዜ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ የሚደረገው ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ የቀረበ ነው፡፡ ከመጠይቁ መላሾች ውስጥ 80% ሁልጊዜ እና አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎቻቸው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡ በሌላ በኩል ለጥያቄ 11 ተማሪዎች በዝምታ እንዲያነቡ የሚደረገው "አልፎ አልፎ ነው" የሚል መልስ የሰጡት 46.7% ሲሆኑ፣ ተማሪዎች በፀጥታ እንዲያነቡ አይደረግም ያሉት ደግሞ 20% ናቸው፡፡

ጥያቄ 10 በጥያቄ 9 ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ መጠይቁን ከሞሉት መምህራን ውስጥ 53.3% ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሚያነቡበት ጊዜ ሲሳሳቱ የንባብ ሂደቱን በማስቆም አስተካክለው እስኪያነቡት ድረስ የተሳሳቱትን እንዲደግሙት እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡ 40% ደግሞ "የንባብ ሂደቱን በማስቆም ራሴ አስተካክየ አነበዋለሁ" በማለት መልሰዋል፡፡ ለጥያቄው "መሳሳታቸውን ያላወቅሁ በመምሰል ንባባቸውን እንዲቀጥሉ አደርጋለሁ" በማለት የመለሱ 6.7% ብቻ ናቸው፡፡ ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ ሲሳሳቱ በዚህ መንገድ ማስተካከልም "አሁን ምን እሳሳት ይሆን?" እያሉ እንዲጨነቁ ሊያደርጋቸው ይችላል፡

ሠንጠረዥ 11፡- አንድ ምንባብ ከመነበቡ በፊት ስለምንባቡ ይዘት በተማሪዎች ሐሳብ የሚሰነዘር ስለመሆኑ የተገኘ መረጃ

| የጥያቄው ተ.ቁ. | ጥያቄ | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 12 | በክፍል ውስጥ ለትምህርት የሚቀርብ ምንባብ ከመነበቡ በፊት ተማሪዎች ስለምንባቡ ይዘተ ነገር ሐሳብ እንዲሰነዝሩ የሚደረገው፣ | | |
| | ሀ. ሁልጊዜ ነው | - | - |
| | ለ. አብዛኛውን ጊዜ ነው | 1 | 6.7 |
| | ሐ. አልፎ አልፎ ነው | 2 | 13.3 |
| | መ. ምንባቡ ከመነበቡ በፊት ተማሪዎች ስለምንባቡ ሐሳብ እንዲሰነዝሩ አይደረግም | 12 | 80.0 |

በሠንጠረዥ 11 እንደሚታየው መጠይቁን ከመለሱት መምህራን ውስጥ 80% ምንባቡ ከመነበቡ በፊት ተማሪዎች ስለምንባቡ ሐሳብ እንዲሰነዝሩ እንደማይደረግ ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን ተማሪዎች ምንባቡ ከመነበቡ በፊት ስለምንባቡ ሐሳብ እንዲሰነዝሩ ቢደረግ ምንባቡን ለመረዳት እንደሚረዳቸው ምሁራን (Statman: 1981፣Nuttal 1982) ይገልጻሉ፡፡

ሐ. <u>በክፍል ሦስት ከቀረቡ ጥያቄዎች የተገኙ መረጃዎች ትንተና</u>

ሠንጠረዥ 12፡- የመማሪያ መጽሐፉ በክፍል ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የሚያዳብሩ ስለመሆናቸው የተገኙ መረጃዎች

| የጥያቄው ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብ | % | ብ | % | ብ | % | ብ | % | ብ | % |
| 1 | በ11ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት <u>ምንባቦች</u> የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያላቸው ብቃት፣ | 1 | 6.7 | 2 | 13.3 | 5 | 33.3 | 4 | 26.7 | 3 | 20 |

| የጥያቄው ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብ | % | ብ | % | ብ | % | ብ | % | ብ | % |
| 2 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የማዳበር ብቃት | - | - | 2 | 13.3 | 5 | 33.3 | 6 | 40 | 2 | 13.3 |
| 6 | በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚጫወተው ሚና ምን ያህል ነው? | 2 | 13.3 | 3 | 20 | 5 | 33.3 | 3 | 20 | 2 | 13.3 |

*ብ = ብዛት

ለ1ኛው ጥያቄ ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ የሚሉትን የመረጡት ብዛት 46.7% ነው፡ ይህም የሌሎቹን ምርጫዎች ከመረጡት አንፃር ሲታይ መጠኑ ከፍተኛ ነው፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት መልመጃዎች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያላቸውን ብቃት በተመለከተ በ2ኛው ተራ ቁጥር ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠው መልስም አሉታዊ ነው፡፡ መጠይቁን ከሞሉት ውስጥ 53.3% መልመጃዎቹ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የማዳበር ብቃታቸው ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የማዳበር ብቃት በተመለከተ በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ የሚል መልስ የሰጡት ብዛት 33.3% ነው፡፡ ጥያቄውን መካከለኛ በማለት የመለሱትም 33.3% ናቸው የቀሩት 33.3% ደግሞ ጥያቄውን ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ በማለት መልሰውታል፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚኙት ምንባቦችና መልመጃዎች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የማዳበር ብቃታቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የማዳበር ብቃት ግን በአብዛኛው መካከለኛ ወይም ከዚያ በላይ እንደሆነ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ሠንጠረዥ 13፡- የተማሪዎችን የማንበብ ልምምድና ፍላጎት በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች

| የጥያቄው ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብ | % | ብ | % | ብ | % | ብ | % | ብ | % |
| 3 | ተማሪዎች በአማርኛ ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት የንባብ ልምምድ፣ | 1 | 6.7 | 3 | 20 | 5 | 33.3 | 4 | 26.7 | 2 | 13.3 |
| 4 | የተማሪዎች በአማርኛ መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ምንባቦች የማንበብ ፍላጎት፣ | 1 | 6.7 | 2 | 13.3 | 4 | 26.7 | 7 | 46.7 | 1 | 6.7 |
| 5 | የተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የመስራት ፍላጎት ምን ያህል ነው | - | - | 3 | 20 | 5 | 33.3 | 5 | 33.3 | 2 | 13.3 |
| 7 | ከሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ውስጥ በክፍል ውስጥ የማንበብ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ብዛት ምን ያህል ነው ? | 2 | 13.3 | 2 | 13.3 | 4 | 26.7 | 4 | 26.7 | 3 | 20 |
| 8 | ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው? | 1 | 6.7 | 2 | 13.3 | 2 | 13.3 | 6 | 40 | 4 | 26.7 |
| 9 | የተማሪዎች በአማርኛ የተጻፉ የተለያዩ ጽሑፎችን የማንበብ ፍላጎት ምን ያህል ነው | - | - | 2 | 13.3 | 4 | 26.7 | 7 | 46.7 | 1 | 6.7 |

ሠንጠረዥ 13 የተማሪዎችን የማንበብ ልምምድ እና ፍላጎት በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎችንና የተሰጡ መልሶችን ይዟል፡፡ በ3ኛው ጥያቄ የተጠሰው መልስ ወደ አሉታዊነት ያደላል፡፡ ተማሪዎች በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ውስጥ የሚያደርጉት የንባብ ልምምድ በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ እንደሆነ የገለጹት 26.7% ሲሆኑ፣ መካከለኛ እንደሆነ የጠቆሙት ደግሞ 33.3% ናቸው፡፡ የቀሩት 40% ግን ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ አመልክተዋል፡፡

ለጥያቄ 4 የተሰጠው መልስም ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ምንባቦች የማንበብ ፍላጎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ለጥያቄው ከተሰጡት መልሶች ውስጥ 53.3% ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ የሚሉ ናቸው፡፡ ተማሪዎች በአማርኛ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የመስራት ፍላጎታቸው ምን ያህል እንደሆነ በ5ኛው ተራ ቁጥር ለቀረበው ጥያቄ 46.7% የሚሆኑት ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

ለ7ኛው ጥያቄ የተሰጠው መልስም ወደ አሉታዊነት ያዘነበለ ነው፡፡ መጠይቁን ከሞሉት ውስጥ 26.7% መካከለኛ ሲሉ፣ 46.7% ደግሞ ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ በማለት መልሰዋል፡፡ በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ በማለት የመለሱት 26.7% ብቻ ናቸው ይህም በክፍል ውስጥ የማንበብ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ቁጥር ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡

8ኛው ጥያቄ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያደርጉትን ጥረት ይመለከታል፡፡ ለጥያቄውም 20% በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ የሚሉትን ሲመርጡ፣ 66.7% ግን ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ የሚሉትን መርጠዋል፡፡ ይህም ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያደርጉት ጥረት ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ያመለክታል፡፡

9ኛው ጥያቄ የተማሪዎችን በአማርኛ የተጻፉ የተለያዩ ጽሑፎችን የማንበብ ፍላጎት ለማወቅ የቀረበ ነው፡፡ ከመጠይቁ መላሾች ውስጥ 53.3% ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ በማለት መልሰዋል፡፡ ጥያቄውን በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ በማለት የመሰሉት 13.3% ብቻ ናቸው፡፡ 26.7% መካከለኛ የሚል መልስ ሲሰጡ፣ የቀሩት 6.7% ግን ለጥያቄው መልስ አልሰጡም፡፡ ለጥያቄው ከተሰጡት መልሶች መረዳት የሚቻለው የተማሪዎች የተለያዩ ጽሑፎችን የማንበብ ፍላጎት ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡

2. የመማሪያ መጽሐፉ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ አያዳብርም በማለት የመለሱ መምህራን የሰጧቸው ምክንያቶች፡-

ሀ. የምንባቦችና የመልመጃዎች ከተማሪዎች ችሎታ በላይ ወይም በታች መሆን

ለ. በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት ምንባቦች የተማሪዎችን የማንበብ በፍላጎት የሚያነሳሱ አለመሆን

ሐ. ከምንባቡ የወጡት አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች መጠየቅን፣ መመራመርን ወዘተ. የሚጠይቁ አለመሆናቸው፡፡

3. የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር በመምህራን የተሰጡ የመፍትሔ ሐሳቦች፡-

ሀ. ተማሪዎች በትርፍ ጊዜያቸው እንዲያነቡ መገፋፋት

ለ. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከሚገኙት ምንባቦች በተጨማሪ ሌሎች ማራኪ፣ የተማሪዎችን ፍላጎት የሚያነሳሱና ችሎታቸውንም የሚመጥኑ ምንባቦችን ለትምህርት ማቅረብ

ሐ. የመማሪያ መጽሐፉን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር በሚያስችል መንገድ እንደገና ማዘጋጀት፡፡

### 4.1.2 <u>ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና</u>

በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ውስጥ አንዱ የተማሪዎችን የንባብ ክሂል ማዳበር እንደሆነ በዚሁ ስራ በመግቢያው ውስጥ ተገልጿል፡፡ የንባብ ክሂልን ማዳበር ከሚያካትታቸው ነጥቦች ውስጥ አንዱ ደግሞ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማዳበር ነው፡፡

ይህንን መሠረት በማድረግም በ11ኛ ክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርቱ እንዴት እንደሚከናወን መረጃ ለማግኘት ሲባል ምልከታዎች ተካሂደዋል፡፡ ከምልከታዎቹ የተገኙት መረጃዎችም እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

ሠንጠረዥ 15፡- ምንባቡ ከመነበቡ በፊት ስለሚከናወኑ ተግባራት የተገኙ መረጃዎች

| ተ.ቁ. | የመምህሩና የተማሪዎች ተግባራት | ድግግም | % |
|---|---|---|---|
| 1 | መምህሩ የምንባቡን ርዕስ ለተማሪዎች ይናገራል፡፡ | 7 | 87.5 |
| 2 | መምህሩ የምንባቡን ርዕስ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጽፋል፡፡ | 5 | 62.5 |
| 3 | መምህሩ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ አዳዲስ ቃላትን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጽል፡፡ | - | - |
| 4 | መምህሩ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ አዳዲስ ቃላትን ፍችዎች ለተማሪዎች ይገልጻል፡፡ | -<br>- | -<br>- |
| 5 | ተማሪዎች ስለምንባቡ መልዕክት ሐሳብ ይሰነዝራሉ፡፡ | | |
| 6 | መምህሩ ለተማሪዎች ምንባቡን የሚያነቡበትን ዓላማ ይገልጽላቸዋል፡፡ | - | - |

በሠንጠረዥ 15 እንደሚታየው በተራ ቁጥር 1 እና 2 የሰፈሩት ነጥቦች ተግባራዊነት አዎንታዊ ነው፡፡ በምልከታው ከተካተቱት መምህራን ውስጥ 87.5% የንባብ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት የምንባቡን ርዕስ ለተማሪዎቻቸው ሲናገሩ፣ 62.5% ርዕሱን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጽፉታል፡፡

በተራ ቁጥር 3 እና 4 የተመለከቱት ነጥቦች ተግባራዊነት ግን ዜሮ ነው፡፡ በምልከታው የታቀፉት መምህራን በሙሉ (100%) የንባብ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት አዳዲስ ብለው የሚገምቷቸውን ቃላት በጥቁር ሰሌዳው ላይ አይጽፉም፤ ፍቻቸውንም ለተማሪዎቻቸው አይገልፁም፤ ተማሪዎችንም የአንዳንድ ቃላትን ፍችዎች እንዲገምቱ አይጋብዟቸውም፡፡

በሠንጠረዡ ተራ ቁጥር 5 እና 6 የተጠቀሱት ቢሆኑም በክፍል ውስጥ ያላቸው ተግባራዊነት ዜሮ ነው፡፡ ምልከታ ከተካሄደባቸው መምህራን ውስጥ 100% ምንባቡን ወደማንበብ ሂደት ሽግግር ከመደረጉ በፊት ተማሪዎች ስለምንባቡ ይዘት (መልዕክት) ሐሳብ እንዲሰነዝሩ ዕድል አይሰጡም፡፡ ተማሪዎች ምንባቡን የሚያነቡበትን ዓላማ ወይም ምንባቡን ካነበቡ በኋላ ምን እንደሚጠበቅባቸው አይገልፁላቸውም፡፡ ይህም ጽሑፉን ምን ያህል ጠለቅ ብለው ማንበብ እንዳለባቸው፣ ካነበቡ በኋላም ምን እንደሚጠበቅባቸው ለማወቅ ችግር ይፈጥርባቸዋል፡፡

ሠንጠረዥ 16፡- ምንባቡ በሚነበብበት ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራትን በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች

| ተ.ቁ. | የመምህሩና የተማሪዎች ተግባራት | ድግግም | % |
|---|---|---|---|
| 7 | መምህሩ ምንባቡን ድምፁን ከፍ አድርጎ ያለምንም ገለጻ (ማብራሪያ) ያነባል፡፡ | 6 | 75 |
| 8 | መምህሩ ድምፁን ከፍ አድርጎ ዐረፍተ ነገር በዐረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ በአንቀጽ እያብራራ (ገለጻ እየሰጠ) ያነባል፡፡ | 2 | 25 |
| 9 | ተማሪዎች በፀጥታ ያነባሉ፡፡ | 2 | 25 |
| 10 | ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ተራ በተራ ያነባሉ፡፡ | 5 | 62.5 |
| 11 | ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሚያነቡበት ጊዜ (የሚያነቡ ከሆነ) ሲሳሳቱ፣ | | |
| 11.1 | መምህሩ ንባባቸውን በማቋረጥ ስህተቱን አስተካክሎ ያነበዋል፡፡ | 2 | 40 |
| 11.2 | አንባቢው ተማሪ ማንበቡን አቋርጦ እንዲያስተካክል በመምህሩ ይነገረዋል፡፡ | 2 | 40 |
| 11.3 | ተማሪው ማንም ጣልቃ ሳይገባበት ማንበቡን ይቀጥላል፡፡ | 1 | 20 |

ሠንጠረዥ 16 አንድ ለትምህርት የሚቀርብ ምንባብ በክፍል ውስጥ በሚነበብበት ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራትን ይመለከታል፡፡ በተራ ቁጥር 7 እንደተገለፀው በምልከታው ከታቀፉት መምህራን ውስጥ 75% ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ያለምንም ማብራሪያ (ገለፃ) ያነባሉ፡፡ ዐረፍተ ነገር በዐረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ በአንቀጽ ማብራሪያና ገለጻ እየሰጡ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ለተማሪዎቻቸው የሚያነቡት ደግሞ 25% ናቸው፡፡

በተራ ቁጥር 9 እና 10 እንደተመለከተው በምልከታው ከተካተቱት መምህራን መካከል 25% ሁሉም ተማሪዎች በአንድነት በፀጥታ እንዲያነቡ ሲያደርጉ፣ 62.5% ደግሞ ተማሪዎቹ ተራ በተራ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያደርጋሉ፡፡

በተራ ቁጥር 11 ስር የሰፈሩት ነጥቦች በ10ኛው ተራ ቁጥር ላይ የተመሰረቱ ሲሆን ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ተራ በተራ በሚያነቡበት ጊዜ ፊደላትንና ቃላትን የመግደፍና አሳስቶ የማንበብ ስህተቶች ሲፈጽሙ መምህራን የሚወስዷቸውን የማስተካከያ እርምጃዎች ለማሰስ የቀረቡ ናቸው፡፡ ተማሪዎችን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ተራ በተራ ከሚያስነብቡት አምስት መምህራን ውስጥ ሁለቱ (40%) የሚያነቡት ተማሪዎች በሚሳሳቱበት ጊዜ የንባብ ሂደቱን በማስቆም (በማቋረጥ) ስህተቱን ራሳቸው አስተካክለው

ያነቡታል፡፡ ተማሪዎቹ ማንበባቸውን አቋርጠው የተሳሳቱትን አስተካክለው እንዲያነቡ የሚያደርጉት ብዛትም ተመሳሳይ (40%) ነው፡፡ በተማሪዎቹ ላይ ጣልቃ ሳይገቡ ተማሪዎቹ ማንበባቸውን እንዲቀጥሉ በፀጥታ የሚከታተሉት መምህራን 20% ብቻ ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 17፡- ምንባቡ ከተነበበ በኋላ ስለሚከናወኑ ተግባራት የተገኙ መረጃዎች

| ተ.ቁ. | የመምህሩና የተማሪዎች ተግባራት | ድግግም | % |
|---|---|---|---|
| 12 | ተማሪዎች ስለተነበበው ምንባብ በጥንድ ወይም በቡድን እርስ በእርስ ይወያያሉ፡፡ | - | - |
| 13 | መምህሩ የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ ለተማሪዎች ይገልጻል፡፡ | 2 | 25 |
| 14 | ተማሪዎች ግልጽ ያልሆነላቸውን ነጥብ መምህሩን ይጠይቃሉ፡፡ | 2 | 25 |
| 15 | መምህሩ ተማሪዎችን የራሱን የቃል ጥያቄዎች ይጠይቃል፡፡ | 2 | 25 |
| 16 | መምህሩ በቀጥታ በመጽሐፉ ውስጥ ወደሚገኙት መልመጃዎች ይሸጋገራል፡፡ | 4 | 50 |
| 17 | የመልመጃዎቹን ጥያቄዎች ተማሪዎች በቃል ይመልሳሉ፡፡ | 2 | 25 |
| 18 | መምህሩ የመልመጃዎቹን ጥያቄዎች በቤት ስራ መልክ ለተማሪዎች ይሰጣል፡፡ | 6 | 75 |

በሠንጠረዥ 17 ውስጥ የተካተቱትን ነጥቦች መሠረት በማድረግ ለትምህርት የቀረበው ምንባብ ከተነበበ በኋላ የሚከናወኑ ተግባራትን ለማሰስ ተሞክሯል፡፡ በተገኘው መረጃ መሠረት የተራ ቁጥር 12 ተግባራዊነት አሉታዊ ነው፡፡ ምንባቡ ከተነበበ በኋላ ተማሪዎች ስለምንባቡ በጥንድም ሆነ በቡድን እርስ በርስ ሀሳብ አይለዋወጡም፡፡ የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ በአጭሩ ለተማሪዎች የሚገልፁት መምህራን ብዛትም 25% ነው፡፡

በምልከታው ውስጥ ከተካተቱት መምህራን ውስጥ 25% ተማሪዎችን የራሳቸውን የቃል አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ሲጠይቁ፣ 50% ደግሞ በቀጥታ በመጽሐፉ ውስጥ ከምንባቡ ቀጥለው ወደሚገኙት መልመጃዎች ይሸጋገራሉ፡፡ ከመምህራኑ ውስጥ 25% ጥያቄዎቹን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እንዲመልሱ ሲያደርጉ 75% ደግሞ ለተማሪዎቹ የቤት ስራ ይሰጧቸዋል፡፡

## 4.1.3 አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ትንተና

የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ማመልከት እንደሆነና ለዚህም መረጃ ለማግኘት ሲባል ሁለት የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች ተዘጋጅተው ተጠኝዎቹ እንዲፈተኗቸው መደረጉ ቀደም ሲል (በ3.2.31) ተገልጿል:: ለጥናቱ የተመረጡት ተጠኝዎች 225 ቢሆኑም ሁለት ተማሪዎች (አንድ ወንድና አንድ ሴት) የመጀመሪያውን ፈተና፣ ሶስት ተማሪዎች (አንድ ወንድና ሁለት ሴቶች) ደግሞ የሁለተኛውን ፈተና ባለመፈተናቸው ከጥናቱ ተወግደዋል:: ስለሆነም ለትንተና የቀረበው የ220 ተማሪዎች ውጤት ነው::

በሁለቱ ፈተናዎች ውስጥ የሚገኙት የምርጫ ጥያቄዎች በአጥኝው ብቻ ታርመዋል:: ነፃ ጥያቄዎቹ ደግሞ በሶስት ምሁራን (በአጥኝው፣ በአንድ የአማርኛ ድህረ ምረቃ ተማሪ እና በአንድ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መምህር) ከታረሙ በኋላ፣ የሶስቱ አራሚዎች አማካይ ውጤቶች ተመዝግበዋል:: በሁለቱም ፈተናዎች ውስጥ የሚገኙት የምርጫ ጥያቄዎች አንድ አንድ ነጥብ ሲሰጣቸው ነፃ ጥያቄዎቹ ደግሞ ሁለት ሁለት ነጥብ ይዘዋል:: በዚህም መሠረት እያንዳንዱ ተማሪ በእያንዳንዱ ፈተና ያገኘው ውጤት ከ15 ታስቦ የሁለቱ ፈተናዎች ውጤት በአንድ ላይ ከ30 ከተደመረ በኋላ ለትንታኔ ያመች ዘንድ ወደ 10 ተለውጧል:: በዚህ መልክ የተገኘው የፈተና ውጤትም የሚከተለውን ይመስላል::

ሠንጠረዥ 18:- በአራሚ አንድ (አጥኝው) የተገኘ ውጤት

| ውጤት | ድግግሞሽ | CF |
|---|---|---|
| 10 | 8 | 8 |
| 9 | 9 | 17 |
| 8 | 21 | 38 |
| 7 | 23 | 61 |
| 6 | 46 | 107 |
| 5 | 46 | 153 |
| 4 | 25 | 178 |
| 3 | 28 | 206 |
| 2 | 9 | 215 |
| 1 | 5 | 220 |
| 0 | 0 | 220 |

የተጠኝዎቹ ብዛት = 220　　　　አማካይ ውጤት = 5.46

የተጠኝዎች ውጤት ድምር = 1202　　　　መደበኛ ልይይት = 2.05

ሠንጠረዥ 19፡- በአራሚ ሁለት የተገኘ ውጤት

| ውጤት | ድግግሞሽ | CF |
|---|---|---|
| 10 | 7 | 7 |
| 9 | 7 | 14 |
| 8 | 19 | 33 |
| 7 | 25 | 58 |
| 6 | 39 | 97 |
| 5 | 55 | 152 |
| 4 | 31 | 183 |
| 3 | 23 | 206 |
| 2 | 10 | 216 |
| 1 | 4 | 220 |
| 0 | 0 | 220 |

የተጠኝዎች ብዛት = 220
አማካይ ውጤት = 5.39

የተጠኝዎቹ ውጤት ጠቅላላ ድምር = 1186
መደበኛ ልይይት = 1.9

ሠንጠረዥ 20፡- በአራሚ ሦስት የተገኘ ውጤት

| ውጤት | ድግግሞሽ | CF |
|---|---|---|
| 10 | 5 | 5 |
| 9 | 7 | 12 |
| 8 | 23 | 35 |
| 7 | 17 | 52 |
| 6 | 43 | 95 |
| 5 | 56 | 151 |
| 4 | 31 | 182 |
| 3 | 24 | 206 |
| 2 | 7 | 213 |
| 1 | 7 | 220 |
| 0 | 0 | 220 |

የተጠኝዎቹ ብዛት = 220
አማካይ ውጤት = 5.35

የተጠኝዎቹ ውጤት ድምር = 1176
መደበኛ ልይይት = 1.95

ሠንጠረዥ 21፡- በሶስቱ አራሚዎች የተገኘ አማካይ ውጤት

| ውጤት | ድግግሞሽ | CF |
|---|---|---|
| 10 | 5 | 5 |
| 9 | 10 | 15 |
| 8 | 21 | 36 |
| 7 | 17 | 53 |
| 6 | 47 | 100 |
| 5 | 55 | 155 |
| 4 | 25 | 180 |
| 3 | 26 | 206 |
| 2 | 9 | 215 |
| 1 | 5 | 220 |
| 0 | 0 | 220 |

የተጠኝዎች ብዛት = 220
የተጠኝዎች ውጤት ጠቅላላ ድምር = 1185

አማካይ ውጤት = 5.40
መደበኛ ልይይት = 1.97

ከዚህ በላይ ከቀረቡት የውጤት ሠንጠረገች መረዳት እንደሚቻለው በሶስቱ አራሚዎች የተገኙት የፈተና ውጤቶች በጣም ተቀራራቢ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በአራሚ አንድ፣ በአራሚ ሁለት እና በአራሚ ሶስት የተገኙ አማካይ ውጤቶች በተከታታይ 5.46፣ 5.39 እና 5.35 ናቸው፡፡ ይህም ከአስተራረምና ከውጤት አሰጣጥ አንጻር በአራሚዎቹ መካከል ከፍተኛ ስምምነት መኖሩን ያመለክታል፡፡

ሠንጠረዥ 22፡- የተጠኝዎችን ውጤት፣ ድግግሞሽ የሚያሳይ

| ውጤት | ብዛት | % |
|---|---|---|
| 10 - 9 | 15 | 6.8 |
| 8 - 7 | 38 | 17.3 |
| 6 - 5 | 102 | 46 |
| 4 - 0 | 65 | 30 |

በሠንጠረዥ 22 እንደተመለከተው ከ10 - 9፣ ከ8 - 7፣ ከ6 - 5 እና ከ4 በታች ውጤት ያገኙት ተማሪዎች ብዛት በተከታታይ 15፣ 38፣ 102 እና 65 ነው፡፡ ይህም

በፐርሰንት ሲታሰብ በቅደም ተከተሉ መሠረት 6.8%፣ 17.3%፣ 46% እና 30% ነው፡፡ ይህም የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ያመለክታል፡፡

### 4.1.3.1 የፆታ እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝምድና ትንተና

ከዚህ ጥናት ንኡሳን ዓላማዎች ውስጥ አንዱ በወንድና በሴት የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች መካከል አንብቦ የመረዳት ችሎታ ልዩነት መኖሩን ወይም አለመኖሩን ማረጋገጥ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት ውስጥ የታቀፉት 99 ሴቶች እና 121 ወንዶች ተማሪዎች መካከል ያለው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ልዩነት እስከምን ድረስ እንደሆነ ለማወቅ ሁለቱ ፆታዎች ያገኙት የፈተና ውጤት በ't-test' ቀመር ተሰልቷል (አባሪ 4.ሐ ን ያገናዝቧል)፡፡ በስሌቱ የተገኘው ውጤትም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ሠንጠረዥ 23፡- የወንድና የቤት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝምድና

| ተጠኝ | Mean | sd | df | tcal | ttab | የልዩነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሴት | 5.54 | 1.84 | 218 | 1.052 | 1.960 | የማያስተማምን |
| ወንድ | 5.26 | 2.06 | | | | |

በሠንጠረዥ 23 እንደተመለከተው የሴት ተማሪዎች አማካይ የፈተና ውጤት 5.54 ሲሆን የወንዶች ደግሞ 5.26 ነው፡፡ በሁለቱ ፆታዎች አማካይ ውጤቶች መካከልም የ 0.28 ልዩነት አለ፡፡ ይህ በሁለቱ ፆታዎች መካከል ያለው የችሎታ ልዩነትም የሚያስተማምን ይሁን የማያስተማምን ለማወቅ ሲባል ለምናልባት ስህተት 5% በመተው ($p < 0.05$) ማለት በ95% እርግጠኝነት በተከሄደው የ't-test' ስሌት የተገኘው የ't cal' ዋጋ (1.052) ለልዩነቱ አስተማማኝነት ተወስኖ ከተቀመጠው የ't tab' ዋጋ (1.960) ያንሳል፡፡ ይህም በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል ያለውና በአማካይ ውጤቶቹ ላይ የታየው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ልዩነት የማያስተማምን መሆኑን ያመለክታል፡፡

### 4.1.3.2 በአማርኛ ቋንቋ አፍ የፈቱና ያልፈቱ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝምድና ትንተና

ከዚህ ጥናት ዓላማዎች ውስጥ አንዱ አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ በፈቱና ባልፈቱ ተማሪዎች መካከል አንብቦ የመረዳት ችሎታ ልዩነት መኖር አለመኖሩን መመርመር ነው፡፡ ይህንን ለማረጋገጥም በዚህ ጥናት ውስጥ የታቀፉት 151 አፋቸውን በአማርኛ የፈቱና አፋቸውን በአማርኛ ያልፈቱ 69 ተማሪዎች በአንብቦ የመረዳት ፈተናዎቹ ያገኙት ውጤት

ሠንጠረዥ 24:- አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱና ያልፈቱ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝምድና ትንተና

| ተጠኝ | Mean | sd | df | t cal | t tab | የልዩነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አፋቸውን በአማርኛ የፈቱ | 5.54 | 2.04 | 218 | 1.725 | 1.960 | የማያስተማምን |
| አፋቸውን በአማርኛ ያልፈቱ | 5.05 | 1.75 | | | | |

$p<0.05$

አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች አማካይ ውጤት 5.54 ሲሆን አፋቸውን በአማርኛ ያልፈቱ ተማሪዎች አማካይ ውጤት ደግሞ 5.05 ነው:: ከአማካይ ውጤት አንፃር በሁለቱ ቡድኖች መካከል ልዩነት ይታያል:: ልዩነቱም 0.49 ነው:: ይህ ልዩነት ማስተማመኑን ወይም አለማስተማመኑን ለማወቅም ለምናልባት ስህተት 5% በመተው በተካሄደው የ't-test'ስሌት የተገኘው የ't cal ዋጋ (1.725) ለልዩነቱ አስተማማኝነት ከተወሰነው የ 't tab' ዋጋ (1.960) አንሶ ይገኛል:: ይህም በዚህ ጥናት ውስጥ በተካተቱት አፋቸውን በአማርኛ የፈቱና ያልፈቱ ተማሪዎች መካከል ያለው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ልዩነት የማያስተማምን መሆኑን ያሳያል::

## 4.2 ማብራሪያ/Discussion/

በመምህራን ተዘጋጅቶ ከሚሰጥ የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት በመነሳት የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ማወቅ እንደሚቻል የተለያዩ ምሁራንን (Nuttal: 1982፣ Narayanaswamy 1975፣ Fry 1963፣ Kavale: 1979) በማጣቀስ ተገልጿል:: ምሁራኑ እንደሚሉት ተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ከፍተኛ ነው የሚባለው ከ10 ከተመዘገበ ፈተና ከ10 - 9 ውጤት ካገኙ ነው:: ችሎታቸው በቂ ነው የሚባለው ደግሞ ውጤታቸው ከ8 - 7 ሲሆን ነው:: ውጤታቸው 6 እና ከዚያ በታች ከሆነ ግን ችሎታቸው ዝቅተኛ ወይም በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል::

ለዚህ ጥናት በተሰጡት ፈተናዎች በሶስቱ አራሚዎች የተገኘውን አማካይ ውጤት በሚያሳየው ሠንጠረዥ 22 እንደተመለከተው በጥናቱ ከታቀፉት 220 ተማሪዎች ውስጥ ከፍተኛ የሚያሰኘውን ውጤት (ከ10 - 9) ያገኙ ተማሪዎች 6.8% ብቻ ናቸው:: በቂ አንብቦ የመረዳት ችሎታን የሚያመለክተውን ውጤት (ከ8 - 7) ያገኙ ተማሪዎች ብዛትም 17.3% ነው:: ከቀሩት ተማሪዎች ውስጥ 46% ዝቅተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታን

የሚገልፀውን ውጤት (ከ6 - 5) አግኝተዋል፡፡ ሌሎቹ 30% ደግሞ በጣም ዝቅተኛ ችሎታን የሚያመለክተውን ውጤት (ከ4 በታች) ያስመዘገቡ ናቸው፡፡

ስለሆነም በዚህ ጥናት የአንብቦ መረዳት የፈተና ውጤት መሠረት አብዛኞቹ /76%/ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ይህም የተማሪዎቻቸውን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተመለከተ መምህራኑ ከሰጡት መልስ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ የተሰራጨላቸውን የጽሑፍ መጠይቅ ሞልተው ከመለሱት መምህራን ውስጥ አብዛኞቹ /60%/ የተማሪዎቻቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነ ገልፀዋል /ሠንጠረዥ 13ን ያገናዝቧል/፡፡

ይህ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤትም ክፍሌ ሀብተማርያም (1986) የተማሪዎችን ሐሳባቸውን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታ በተመለከተ ባካሄደው ጥናት ካገኘው ውጤት ጋር ተመሳሳይ ሆኗል፡፡ በክፍሌ ሀብተማርያም ጥናት መሠረት በናሙናነት ከተመረጡት ተማሪዎች ውስጥ 84.19% ዓረፍተ ነገር የመጻፍ ችሎታን ለመመዘን በተሰጠው ፈተና 6 እና ከዚያ በታች ውጤት አግኝተዋል፡፡ የተማሪዎቹ አንቀጽ የመጻፍ ችሎታም ቢሆን ዝቅተኛ እንደሆነ ጥናቱ አመልክቷል፡

በዚህ ጥናት ውስጥ በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል አንብቦ የመረዳት ችሎታ ልዩነት መኖሩን ወይም አለመኖሩን ለማየት ሲባል የሁለቱ ፆታዎች ውጤት በ′t-test′ ቀመር ተሰልቷል ( አባሪ 4 ሐን ይመለከቷል)፡፡ በጥናቱ ውስጥ በተካተቱት የወንድና የሴት ተማሪዎች የፈተና ውጤት መሠረትም ጾታ በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ አላደረገም፡፡ ይህም በድሉ ዋቅጅራ (1988) ባካሄደው ጥናት ካገኘው ውጤት ጋር ስምም ሆኗል፡፡ በድሉ በኮሌጅ ተማሪዎች ላይ ባካሄደው ጥናት በጥናቱ ውስጥ ባካተታቸው ወንድና ሴት ተማሪዎች መካከል ያለው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከግንዛቤ የማይገባ እንደሆነ አመልክቷል፡፡

አፋቸውን በአማርኛ በፈቱና በአማርኛ ባልፈቱ ተማሪዎች መካከል ያለው አንብቦ የመረዳት ችሎታ እስከምን ድረስ እንደሆነም ተመርምሯል፡፡ በተካሄደው የ′t-test′ ስሌት (አባሪ 4 መን ይመለከቷል) ውጤት መሠረትም አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ በፈቱና ባልፈቱ ተማሪዎች መካከል ያለው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ልዩነት ከግንዛቤ የሚገባ (የሚያስተማምን) ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህ ጥናት አቅራቢ እምነት መሠረት አፋቸውን በአማርኛ በፈቱና በአማርኛ ባልፈቱ ተማሪዎች መካከል ያለው አንብቦ የመረዳት ችሎታ የሚያስተማምን ያልሆነበት ምክንያትም በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን ያልፈቱ ተማሪዎችም

ቢሆኑ በቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ ውስጥ ስለሚኖሩና አፋቸውን እንደፈቱበት ተማሪዎች በዕለት ተዕለት ስለሚገለገሉበት ሊሆን ይችላል፡፡

በአጠቃላይ፣ ወደ ተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ስንመለስ በዚህ ጥናት ከታቀፉት ተማሪዎች ውስጥ 76% የሚሆኑት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ከፍ ሲል ተገልጿል፡፡ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከሚወሰንባቸው ነጥቦች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ደግሞ በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የቋንቋ ትምህርት ነው (Getachew: 1996፣ በድሉ 1988)፡፡ የአማርኛ ቋንቋ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሚሰጥባቸው ዓላማዎች ውስጥ አንዱ የማንበብ ክሂልን ማዳበር እንደሆነም በቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት ላይ ተገልጾ ይገኛል፡፡ የማንበብ ክሂል ከሚያካትታቸው ውስጥ አንዱ ደግሞ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ፈተናዎች ያገኙት ውጤት የሚያመለክተው ትምህርቱ የተማሪችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ አለማዳበሩን ነው፡፡ ስለሆነም ከዚህ በታች የክፍሉ ውስጥ የንባብ ትምህርት እንዴት እንደሚካሄድ ለመግለጽ ይሞከራል፡፡

አንድ ምንባብ በክፍል ውስጥ በሚቀርብበት ጊዜ፣ ምንባቡን ወደ ማንበብ ሂደት ሽግግር ከመደረጉ በፊት ተማሪዎች ስለርዕሱ ቀድሞ ካላቸው እውቀት በመነሳት የምንባቡ መልዕክት ምን ሊሆን እንደሚችል ሀሳብ ቢሰነዝሩ ጽሑፉን በሚያነቡበት ጊዜ ፍፁም አዲስ መስሎ እንዳይሰማቸው ይረዳቸዋል (Williams: 1984፡ 7፣ Nuttal:1982፡ 154)፡፡ ከዚህ ባሻገርም በምንባቡ ውስጥ ያሉ የምንባቡን መልዕክት ለመረዳት እንቅፋት የሚሆኑ አንዳንድ አዳዲስ ቃላት ለተማሪዎቹ በቅድሚያ ሊገለፁላቸው ይገባል (Statman: 1981፡ 232፣ Nuttal: 157)፡፡ ተማሪዎቹ ጽሑፉን የሚያነቡበትን ዓላማ መግለጽም በቅድመ ንባብ ወቅት ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል አንዱ እንደሆነ ምሁራኑ (Nuttal 153፣ Williams: 1991፡ 7) ያስገነዝባሉ፡፡ ይህም ተማሪዎቹ ምንባቡን ምን ያህል ጠለቅ ብለው ማንበብ እንዳለባቸው ለመወሰን ይረዳቸዋል፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ በተካተቱት ትምህርት ቤቶች ግን ይህ ተግባራዊ እንደማይሆን ለመምህራን ከተሰራጨው መጠይቅና በክፍል ውስጥ ከተካሄደው ምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ምልከታ ከተደረገባቸው ክፍለ ትምህርቶች ውስጥ በማንኛውም ቢሆን ምንባቡ ከመነበቡ በፊት ተማሪዎቹ ካላቸው ቅድመ ዕውቀት /background knowledge/ በመነሳት ስለምንባቡ ሐሳብ እንዲሰነዝሩ ሲደረግ አልታየም፡፡ ምልከታ ከተካሄደባቸው መምህራን ውስጥ አብዛኞቹ ወደ ማንበቡ ሂደት የሚሸጋገሩት የምንባቡን ርዕስ ለተማሪዎቹ በቃል በመግለጽ ወይም በጥቁር ሰሌዳው ላይ በመጻፍ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ አልፈው ግን ከዚህ

በላይ ጽሑፉን አንብበው ለመረዳት ተማሪዎችን ያግዛሉ የተባሉ ተግባራትን (ለምሳሌ ጽሑፉ የሚነበብበትን ዓላማ መግለጽ፣ ስለ ጽሑፉ ሐሳብ መሠንዘር፣ ወዘተ፡) እንዲከናወኑ አያደርጉም፡፡

ብዙ ምሁራን በሚቀበሉት ባለ ሶስት ደረጃ (three phase) የንባብ ትምህርት አቀራረብ መሠረት ለትምህርት የቀረበው ምንባብ በሚነበብበት ጊዜ መከናወን ስላለባቸው ጉዳዮችም ምሁራኑ የሚሰነዝሯቸው አስተያየቶች አሉ፡፡ ከሁሉም በፊት ተማሪዎች የተለያዩ ጽሑፎችን አንብበው መረዳት ይችሉ ዘንድ፣ በክፍል ውስጥ በቂ ልምምድ ማድረግ አለባቸው፡፡ የመምህሩ ሚና ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ ድጋፍ መስጠት፣ ማንበባቸውን መከታተል፣ የክፍሉን ሁኔታ መቆጣጠር ነው (Silberstein: 1987፡ 32)፡፡

ይሁን እንጅ በምልከታው ማረጋገጥ እንደተቻለው የመምህራን ሚና በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ በምልከታው የታቀፉት መምህራን በሙሉ በክፍል ውስጥ ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ለተማሪዎቻቸው ያነባሉ፡፡ ከመምህራኑ ውስጥ 25% ምንባቡን ዐረፍተ ነገር በዐረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ በአንቀጽ ማብራሪያ እየሰጡ ያነቡታል፡፡ ስለሆነም መምህራን የሚያከናወኑት ተማሪዎች ሊያከናውኑት የሚገባውን ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ተማሪዎች አንድ ለትምህርት የቀረበ ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ በፀጥታ ቢሆን እንደሚሻል የመስኩ ባለሙያዎች (Greenwood 1981፡ 82) ያስገነዝባሉ፡፡ በገሀዱ ዓለም የዕለት ተዕለት ህይወታችን የምናነበው በፀጥታ ከመሆኑ ባሻገር፣ በተለይም ጽሑፉ የሚነበብበት ዓላማ መልዕክቱን ለመረዳት ከሆነ መነበብ ያለበት በፀጥታ ነው (Getachew: 1996፡ 26፡ Molla:1987፡ 5፣ Lewis እና Jimmie 1985፡ 111፣ Nuttal: 1982፡ 21)፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ ማረጋገጥ እንደተቻለው ግን አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎቹ እንዲያነቡ በሚደረግበት ጊዜ የሚያነቡት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ነው፡፡ በምልከታው ከታቀፉት መምህራን ውስጥ ተማሪዎቻቸውን ተራ በተራ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ የሚያደርጉት 62.5% ሲሆኑ፣ ተማሪዎቹ ምንባቦቹን በፀጥታ እንዲያነቡ የሚያደርጉ መምህራን ግን 25% ናቸው፡፡ ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሚያነቡበት ጊዜም ፊደላትንና ቃላትን ሲገድፉ ወይም አሳስተው ሲያነቡ መምህሩ ንባባቸውን በማቋረጥ ራሱ አስተካክሎ ያነበዋል፤ ወይም ተማሪዎቹ እንደገና አስተካክለው እንዲያነቡ ያደርጋል፡፡ እንደጥናቱ አቅራቢ እምነት፣ አንባቢው ተማሪ በሚሳሳትበት ጊዜ

በተደጋጋሚ በዚህ መንገድ ለማስተካከል መሞከር አንባቢው "አሁን ምን እሳሳት ይሆን ?" እያለ እንዲጨነቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ይህም ጽሑፉን የመረዳት አቅሙን ይገድብበታል፡፡

አንድ ለትምህርት የቀረበ ምንባብ ከተነበበ በኋላ የሚከናወኑት ተግባራት ተማሪዎች ምንባቡን የበለጠ እንዲረዱት የሚያስችሉ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ከምንባቡ በኋላ የሚቀርቡት ጥያቄዎችና ውይይቶች ዋነኛ ዓላማም አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማዳበር ነው (Greenwood: 1981፡ 83፣ Nuttal: 1982)፡፡ በተለይም ምንባቡ ከተነበበ በኋላ ተማሪዎች በጥንድ ወይም በቡድን ውይይት ቢያካሂዱ ምንባቡን የበለጠ ይረዱታል፡፡ ይህ አለመደረጉን ግን ከምልከታው ማወቅ ተችሏል፡፡ አብዛኞቹ መምህራን ተማሪዎቹ ስለተነበበው ምንባብ እንዲወያዩ አያደርጉም፡፡ አንድ ምንባብ ከተነበበ በኋላ ተማሪዎችን የራሳቸውን የቃል ጥያቄ የሚጠይቁት መምህራንም ቢሆኑ አነስተኛ (12.5%) ናቸው፡፡ አብዛኞቹ መምህራን ምንባቡ ተነቦ እንዳበቃ በቀጥታ በመጽሐፉ ውስጥ ወደሚገኙት መልመጃዎች ይሸጋገራሉ፡፡ ከመምህራኑ ውስጥ 75% በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙትን አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች በቤት ስራነት ለተማሪዎቻቸው ሲሰጡ 25% ደግሞ በክፍል ውስጥ በቃል እንዲመለሱ ያደርጋሉ፡፡ ተማሪዎች በቤት ስራነት የተሰጧቸውን ጥያቄዎች ራሳቸው ይስሯቸው ወይም መልሶቻቸውን ከሌሎች ጓደኞቻቸው ይገልብጧቸው ማወቅም አስቸጋሪ ነው፡፡

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ምንባቦችም ሆኑ መልመጃዎች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያላቸው ብቃት ዝቅተኛ እንደሆነ መጠይቁን ሞልተው የመለሱት መምህራን ገልፀዋል፡፡ ምንባቦቹ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጐት አያነሳሱም፣ የተደጋጋሚ ባህሪ ስላላቸው ለማንበብ ያሰለቻሉ፣ ወዘተ. የሚሉት በመምህራን ከተሰጡት መልሶች መካከል በአብነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ስለሚገኙት ምንባቦችና መልመጃዎች መምህራኑ እነዚህንና የመሳሰሉትን መልሶችና አስተያየቶች ይስጡ እንጅ በምልከታ የታቀፉት መምህራን ከመማሪያ መጽሐፉ ውጭ ሌሎች ምንባቦችንና የራሳቸውን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች እንደማያቀርቡ ታይቷል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5. ማጠቃለያና አስተያየት

### 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ነው የሚለውን አስተያየት ምን ያህል እውነት እንደሆነ ለማረጋገጥ የተካሄደ ነው፡፡ ለዚህም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ የመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በናሙናነት በተመረጡት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማሰስ ተሞክሯል፡፡ በናሙናነት ከተመረጡት ተማሪዎች ውስጥ አብዛኞቹ በተሰጡት አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች ያገኙት ውጤት ዝቅተኛ ነው፡፡ ስለሆነም በጥናቱ የተካተቱት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ከጥናቱ ውጤት ለመረዳት ተችሏል፡፡

የአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ዓላማዎች ተነድፈውለት በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በትምህርትነት በመሰጠት ላይ እንደሚገኝ በዚህ ስራ መግቢያ (1.1) ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ ከአጠቃላይ ዓላማዎቹ ውስጥ አንዱ የተማሪዎችን የንባብ ክሂል ማዳበር የሚለው ነው፡፡ በንባብ ክሂል ከሚካተቱት ውስጥ አንደኛው ደግሞ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማዳበር ነው፡፡ በጥናቱ የተካተቱት ተማሪዎች በተሰጧቸው አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች ዝቅተኛ ውጤት ማግኘትም ይህ ዓላማ ከግብ እንዳልደረሰ ያሳያል፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከፆታ እና ከአፍ መፍቻ ቋንቋ አንጻር ተመርምሯል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተውም ከፆታም ሆነ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ አንፃር የችሎታ ልዩነት የለም፡፡ በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት ወንዶችም ሆኑ ሴቶች፣ አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱም ሆኑ ያልፈቱ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ተመሳሳይ ነው፡፡ በገጽ 14፣ ሠንጠረዥ 1 በተጠቆመው መመዘኛ እና በገጽ 42፣ ሠንጠረዥ 22 በተቀመጠው ውጤት መሠረት የሁሉም ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ እንዲሆን ከሚያደርጉት ነጥቦች ውስጥ የመማሪያ መጽሐፉ እና በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የንባብ ትምህርት በዋነኛነት ይጠቀሳሉ፡፡ ስለሆነም የመማሪያ መጽሐፉን ብቃት በሚመለከት ለመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ተሰራጭቷል፡፡ በክፍል ውስጥ የሚካሄደው የንባብ

ትምህርትም እንዴት እንደሚከናወን ለማሰስም ከተሰራጨው የጽሑፍ መጠይቅ በተጨማሪ የክፍል ውስጥ ምልከታ ተካሂዷል፡፡ ከጽሑፍ መጠይቁም ሆነ ከምልከታው ማረጋገጥ እንደተቻለው የመማሪያ መጽሐፉ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ብቃት የለውም፡፡ በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የንባብ ትምህርትም ቢሆን የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማዳበር የሚያስችል አይመስልም፡፡ በትምህርቱ ወቅት አብዛኞቹ ተግባራት የሚከናወኑት በተማሪዎች ሳይሆን በመምህሩ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ በክፍል ውስጥ ለትምህርት የቀረበውን ምንባብ መምህሩ ሲያነብ ተማሪዎች ያዳምጣሉ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች እያዳመጡ መሆናቸውንም መምህሩ አይከታተልም፡፡ ስለሆነም መምህሩ ሲያነብ የተወሰኑ ተማሪዎች ሌሎች ተግባራትን (ለምሳሌ የተለያዩ የቤት ስራዎችን መስራት፣ ከጓደኛ መገልበጥ፣ ሌሎች ጽሑፎችን ማንበብ ወዘተ.) እንደሚያከናውኑ በምልከታው ተረጋግጧል፡፡

የመምህሩ ተግባር ለተማሪዎች ድጋፍ መስጠት፣ ችግር ሲገጥማቸው መርዳት፣ የክፍሉን ውስጥ ሁኔታ መቆጣጠር እንጅ፣ በተማሪዎች መከናወን የሚገባቸውን ተግባራት መፈፀም መሆን የለበትም፡፡ አብዛኞቹ ተግባራት በተማሪዎች መከናወን ይገባቸዋል፡፡ ይሁን እንጅ፣ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ የንባብ ልምምድ ውሱን ነው፡፡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚቀርቡትን ምንባቦች እንዲያነቡ የሚደረገው አልፎ አልፎ ነው፡፡ አልፎ አልፎ በሚያነቡበት ጊዜም ፊደላትን የመግደፍ፣ ቃላትን አሳስቶ የማንበብ፣ የሚጠብቀውን የማላላት ወይም የሚላላውን የማጥበቅ እና የመሳሰሉትን ስህተቶች ሲፈጽሙ መምህሩ ጣልቃ እየገባ ያስተካክልላቸዋል፤ ወይም እንደገና አስተካክለው እንዲያነቡ ይነግራቸዋል፡፡ ይህም ተማሪዎቹ የጽሑፉን መልዕክት ለመረዳት ከማተኮር ይልቅ "ተሳሳትኩ አልተሳሳትኩ" እያሉ እንዲጨነቁ ያደርጋቸዋል፡፡ ጭንቀታቸው ትኩረታቸውን ይበትንባቸዋል፤ ሊኮተኮት የሚገባውን የማስተዋል ችሎታ ያጠወልገዋል፡፡

ከዚህ ጥናት መረዳት እንደተቻለው በክፍል ውስጥ ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ በአብዛኛው ተግባራዊ የሚሆነው በፀጥታ ከማንበብ ይልቅ ድምጽን ከፍ አድርጎ የማንበብ ስልት ነው፡፡ እንደአስፈላጊነቱ ሁለቱንም ተግባራዊ ማድረግ ቢቻልም፣ ብዙ ጊዜ መበረታታት ያለበት የፀጥታ ንባብ መሆን እንደሚገባው የመስኩ ባለሙያዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ይህም በሀገራችን በአማርኛ ቋንቋ ንባብን በማስተማር ሂደቱ ጥናት ሊካሄድበት የሚገባ ቢሆንም፣ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በማስነበብ ላይ ብቻ የሙጥኝ ማለት የለባቸውም፡፡ ተማሪዎች አንድን ጽሑፍ በዝምታ በማንበብ መረዳት ይችሉ ዘንድ በቂ ልምምድ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት ምንባቦችም ሆኑ መልመጃዎች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የማዳበር ብቃታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉት መምህራን ገልፀዋል:: ይሁን እንጅ፣ በናሙናነት የተመረጡት መምህራን ከመጽሐፉ ውጭ ይሻላሉ የሚሏቸውን ሌሎች ምንባቦች ለትምህርት እንደማያቀርቡ፣ የራሳቸውን አንብቦ የመረዳት መልመጃዎችም እንደማይሰጡ በምልከታው ተረጋግጧል:: በናሙናነት ተመርጠው ሲያስተምሩ ምልከታ የተካሄደባቸው መምህራን የሚያስተምሩት በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ብቻ በመመስረት ነው:: መጽሐፉ ብቃት እንደሌለው እስካመኑ፣ ምንባቦቹና መልመጃዎቹም የተማሪዎችን ፍላጎት አያነሳሱም፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታን የማዳበር ብቃታቸውም ዝቅተኛ ነው እስካሉ ድረስ ሌሎች ብቁ ናቸው፣ የተማሪዎችን ፍላጎት ያነሳሳሉ፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታንም ያዳብራሉ የሚሏቸውን ጽሑፎች እያሰባሰቡ ለትምህርት ማቅረብ ይጠበቅባቸው ነበር::

በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችም ብዙ ጊዜ ለተማሪዎች በቤት ሥራነት እንደሚሰጡ በምልከታ ተረጋግጧል:: ነገር ግን ተማሪዎች ጥያቄዎቹን ከጓደኞቻቸው ይገልብጧቸው ወይም እራሳቸው ምንባቡን አንብበው በተረዱት መሰረት ይስሯቸው ማወቅ ያስቸግራል:: ስለተማሪዎች ከሚባለውና ከምናውቀውም ኩረጃ ያደርጋሉ ማለት አጉል ግምት አይሆንም::

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትና የመሳሰሉት ሁሉ በአንድነት የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዲገኝ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱ የዚህ ጥናት አቅራቢ ያምናል::

## 5.2 አስተያየት

የጥናቱ አቅራቢ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር አስተዋጽኦ ያደርጋሉ በማለት የሚከተሉትን አስተያየቶች ይሰነዝራል::

ሀ. መምህራኑ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ንባብን እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል::

ለ. መምህራኑ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ብቻ ከመመካት ይልቅ የተለያዩ ምንባቦችን በማሰባሰብ ማቅረብ ይኖርባቸዋል::

ሐ. በክፍል ውስጥ በሚደረገው የንባብ ትምህርት ተማሪዎች ሙሉ ተሳትፎና በቂ ልምምድ ማድረግ አለባቸው::

መ. የፀጥታ እና ድምጽን ከፍ አድርጎ የማንበብ ጠቀሜታና በክፍል ውስጥ በምን መልክ መቀናጀት እንዳለባቸው በሌሎች አጥኝዎች ጥናት ሊካሄድ ይገባል፡፡

ሠ. የተማሪዎችን በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚያስችል የማስተማር ዘዴ በተመራማሪዎች ተጠንቶ ቢቀርብ ችግሩ ሊቃለል ይቻላል፡፡

# ዋቢዎች (Bibliography)

Carrel, P.L. et al (eds.). 1988. *Interactive approach to second language reading.* Cambridge university press.

Connor, Ulla and Charless Read. 1978. "passage dependency in ESL reading comprehension tests." *Language learning,* 28 (1), pp. 149 - 162.

Davey, Beth. 1987. "Relations between word knowledge and Comprehension: Generalizations across tasks and readers." *Journal of Educational research,* 80 (3), pp. 179 - 183.

Ellis Rod and Brain Tomlison. 1980. *Teaching Secondary English: a guide to the teaching English as a second language.* Longman.

Fry, E. 1963. *Reading faster. A drill book.* Cambrfidge university press.

Gage, N.C. 1963. *Handbook of research on teaching.* Chicago: Rand Mc Nally and Co.

Getachew Asrate. 1996. "The teaching of reading in government high schools in A.A: A discriptive study." unpublished M.A. theses, Addis Ababa University.

Getachew Dinku. 1993. "The use of pre-,while - and post reading activities in teaching reading in grade 9." unpublished B.A thesis, Addis Ababa University.

Grabe, W. 1988. "Reassessing the term interactive." in P.L. Carrel, et al (eds.) pp. 56 - 70.

Greenwood, J. 1981. "Comprehension and reading." in *The teaching of English as an international language: practical guide.* G abbot and p. wangard (eds.) pp. 81 - 110.

Grellet, F. 1981. *Developing reading skills: A practical guide to reading comprehension exercises.* Cambridge: Cambridge University Press.

Griffin, S.M. 1992. "Reading Aloud." *TESOL Quarterly,* 26(4), pp. 784 - 86.

Harris, A.J. 1965. *How to increase reading ability.* Newyork: David and Mckay Company.

Harrison, A. 1983. *A Language Testing Handbook*. Mc - Millan Publishers Ltd.

Heaton, J.B. 1975. *Writing English Language Tests: A Practical guide for teachers of English as a second language of foreign language*. Longman.

__________1988. *Writing English language Tests*. London: Longman.

__________1990. *Classroom Testing*. London: Longman.

Heining, G.H. 1975. "Measuring foreign language reading comprehension." *Journal of reading*, 25(1), pp. 109 - 121.

Hughes, A. 1995. *Testing for language teachers*. Cambridge University Press.

Jonathan, A. 1971. "A technique for measuring reading comprehension and readability." *Journal of English language teaching*, 25 (2), pp. 178 - 182.

Kavale, K. 1979. "Selecting and evaluating reading tests." in *Reading tests and teachers: A practical guide*. R. Schreir (ed.), pp. 9 - 32.

Langmuir, charles and John Bowers. 1967. "English language reading ability of HSIU Freshman and law students." HSIU (Memographed).

Lewis, M. and Jimmie, H. 1985. *Practical guides for language teaching*.London: Language teaching publications.

Madson, H.S. 1970. "Coping with English language Transition problems at secondary and university levels." HSIU, (Memographed).

__________1983. *Techniques in testing*. Oxford Printing press.

Marks, E. and Nou, A. 1967. "procedures and criteria for Evaluating Reading and Listening comprehension test. "*Journal of Education and Psychology measurement*, 27(2), pp. 335-348.

Molla Jembere. 1987. "Addis Ababa University Freshman students' reading speed in English language." Unpublished M.A. thesis, Addis Ababa University.

Narayanaswamy, K.R. 1975. "The measurement of reading ability." *Journal of English language teaching*, 29 (2), pp. 143 - 150.

Narayanaswamy, K.R. 1972. "An experiment in reading comprehension at the colledge level." *Journal of English language teaching*, 26 (2).

Nuttal, Christine. 1982. *Teaching reading skills in a foreign language*. London: Heinemann educational books.

Schreir, K. (ed). 1979. *Reading tests and teachers:A practical guide*. International reading association.

Silberstein, S. 1987. "let's take an other look at reading: Twenty - five years of reading instruction.*Forum*, 25(4), pp. 784 - 786.

Statman, S. 1981. "The activation of systematic theory: A pedagogical theory in the EFL classroom." *Journal of English language teaching*, 35(3), pp. 232 - 233.

Stavans, A. and Brenda,O.1993. "Assessing EFL reading comprehension: The cause of Ethiopian learners." *System*, 21 (4), pp. 481 - 491.

Tabia, A.R. 1996. "Comprehension through pictures.*Forum*,34(1).

Weir, C.J. 1990. *Communicative Language Testing*. Newyork: printice Hall.

Williams, D. 1983. "Developing reading skills at the post primary level." *Forum* 21 (3).

Williams, E. 1984. *Reading in the language classroom*. London: MeMillan publishes Ltd.

____________ . 1993. "First and Second language reading proficiency of year 3,4, and 6 children in Malawi and Zambia." *Journal of reading in a foreign language*, 10(1), pp. 915 - 930

በየነ ማሞ፣ 1985:: "በዘጠኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች የቋንቋውን ክሂሎች የሚያዳብሩ ናቸው?"::ለአማርኛ ማስተማር ማስትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ::

በድሉ ዋቅጅራ፣ 1988:: "ተሳታፊነት-ጭምትነት የስብዕና ዓይነት ከድርሰት መጻፍና ከአንብቦ መረዳት ጋር ያለው ተዛምዶ፤በሶስት ኮሌጆች ተማሪዎች ላይ የተደረገ ጥናት::" ለአማርኛ ማስተማር ማስትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ አዲስ አበበ ዩኒቨርስቲ::

ተስፋዬ ሸዋየ፣ 1986:: *አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታን ማዳበር*:: አዲስ አበባ፤ ት.መ.ማ.ማ.ድርጅት::

ትምህርት ሚኒስቴር፣ 1970:: *የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት (ከ7 - 12ኛ ክፍል)*:: አዲስ አበባ፤ በሥርዓተ ትምህርት ሱፖርቪዥን መምሪያ የአማርኛ ትምህርት ቡድን የተዘጋጀ::

__________፣ 1984:: *የአማርኛ ቋንቋ ሲለበስ ከ9-12 ክፍል*:: አዲስ አበባ፤ ት.መ.ማ.ማ.ድርጅት::

ክፍሌ ሀብተማርያም፣ 1986:: "የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሐሳባቸውን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታ::" ለአማርኛ ማስተማር ማስትሬት ዲግሪ የቀረበ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ::

ጌታቸው አዱኛ፣ 1986:: "ለአስረኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች የብቃት ደረጃ::" ለአማርኛ ማስተማር ማስትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ::

# አባሪዎች

አባሪ 1:- ለመምህራን የተሰራጨ የጽሑፍ መጠይቅ

## በሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መምህራን የሚሞላ መጠይቅ

ይህ የጽሑፍ መጠይቅ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚገኙ የመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጥናት የተዘጋጀ ነው:: ጥናቱ የታለመውን ግብ ሊመታ የሚችለውም ትክክለኛ መረጃ ማሰባሰብ ሲቻል ነው:: መጠይቁን በግዴለሽነት መሙላትም በጥናቱ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል:: ስለሆነም መጠይቁን በጥንቃቄ ይሞሉ ዘንድ በትህትና እየጠየቅሁ ለትብብርዎ አመሰግናለሁ::

<u>ክፍል አንድ፡- </u>አጠቃላይ መረጃዎች

ከዚህ በታች ያሉትን ባዶ ቦታዎች ትክክለኛ መረጃዎችን በመጻፍ ይሙሉ፡፡

1. ጾታ ______________
2. የትምህርት ደረጃ ________________
3. የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት ______________________
4. የአገልግሎት ዘመን ________________________________
5. የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ ________________________

<u>ክፍል ሁለት</u>

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት ምርጫዎች መካከል የሚስማሙበትን ምርጫ የሚያመለክተውን ሆሄ እየመረጡ በመክበብ ያመልክቱ፡፡

1. በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ የሚቀርበው ትምህርት ይበልጥ የሚያተኩረው በየትኛው ክሂል ላይ ነው ?
   ሀ. በማዳመጥ
   ለ. በመናገር
   ሐ. በማንበብ
   መ. በመጻፍ
2. በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከሚከተሉት ውስጥ ይበልጥ የሚያጎለብተው የትኛውን ነው ?
   ሀ. አዳምጦ የመረዳት ችሎታን
   ለ. ሐሳብን በንግግር የመግለጽ ችሎታን
   ሐ. አንብቦ የመረዳት ችሎታን
   መ. ሐሳብን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታን
3. ለሚያስተምሯቸው ተማሪዎች መልመጃዎችን ምን ያህል ይሰጣሉ ?
   ሀ. ሁልጊዜ እሰጣለሁ
   ለ. አብዛኛውን ጊዜ እሰጣለሁ
   ሐ. አልፎ አልፎ እሰጣለሁ

4. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት መልመጃዎች ከሚከተሉት ውስጥ ይበልጥ የሚያተኩሩት በየትኛው ላይ ነው ?
   ሀ. አዳምጦ በመረዳት
   ለ. ሀሳብን በንግግር በመግለጽ
   ሐ. አንብቦ በመረዳት
   መ. ሀሳብን በጽሑፍ በመግለጽ
5. ለተማሪዎች የሚሰጧቸውን መልመጃዎች ምን ያህል ተከታትለው ያርማሉ?
   ሀ. ሁልጊዜ
   ለ. አብዛኛውን ጊዜ አርማለሁ
   ሐ. አልፎ አልፎ አርማለሁ
6. ከሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ውስጥ በየጊዜው የሚሰጧቸውን መልመጃዎች የሚሰሩ ምን ያህሉ ናቸው?
   ሀ. ሁሉም ይሰራሉ
   ለ. አብዛኞቹ ይሰራሉ
   ሐ. ጥቂቶቹ ይሰራሉ
7. ተማሪዎች ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ የሚደረገው
   ሀ. ሁልጊዜ ነው
   ለ. አብዛኛውን ጊዜ ነው
   ሐ. አልፎ አልፎ ነው
   መ. በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ አይደረግም
8. ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ካሉት ውጭ ሌላ ተጨማሪ ምንባቦችን የሚያነቡት፣
   ሀ. ሁልጊዜ ነው
   ለ. አብዛኛውን ጊዜ ነው
   ሐ. አልፎ አልፎ ነው
   መ. ሌሎች ተጨማሪ ምንባቦችን አያነቡም
9. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በየተራ እንዲያነቡ የሚደረገው፣
   ሀ. ሁልጊዜ ነው
   ለ. አብዛኛውን ጊዜ ነው
   ሐ. አልፎ አልፎ ነው
   መ. በፍፁም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በየተራ እንዲያነቡ አይደረግም

10. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች በየተራ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ የሚያደርጉ ከሆነ በሚያነቡበት ጊዜ ሲሳሳቱ ምን እርምጃ ይወስዳሉ?

ሀ. አስተካክለው እስከሚያነቡት ድረስ የተሳሳቱትን እንዲደግሙት አደርጋለሁ፡፡

ለ. የንባብ ሂደቱን በማቋረጥ ስህተቱን እራሴ አስተካክዬ አነባለሁ፡፡

ሐ. መሳሳታቸውን ያላወቅሁ በመምሰል ንባባቸውን እንዲቀጥሉ አደርጋለሁ፡፡

11. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች ድምፃቸውን ሳያሰሙ (በዝምታ) እንዲያነቡ የሚደረገው፣

ሀ. ሁልጊዜ ነው

ለ. አብዛኛውን ጊዜ ነው

ሐ. አልፎ አልፎ ነው

መ. በፍፁም ድምፃቸውን ሳያሰሙ (በዝምታ) እንዲያነቡ አላደርግም፡፡

12. በክፍል ውስጥ አንድ ለትምህርት የሚቀርብ ምንባብ ከመነበቡ በፊት ከምንባቡ ርዕስ በመነሳት ተማሪዎች ስለምንባቡ ይዘት ነገር ሐሳብ እንዲሰነዝሩ የሚደረገው፣

ሀ. ሁል ጊዜ ነው

ለ. አብዛኛውን ጊዜ ነው

ሐ. አልፎ አልፎ ነው

መ. በፍፁም ምንባቡ ከመነበቡ በፊት ተማሪዎች ስለምንባቡ ሀሳብ እንዲሰነዝሩ አይደረግም፡፡

<u>ክፍል ሶስት</u>፡

ከዚህ በታች ለቀረቡት ሐሳቦችና ጥያቄዎች አምስት አምስት መመዘኛዎች ተሰጥተዋል፡፡ ለየሐሳቦቹና ጥያቄዎቹ ከተሰጡት መመዘኛዎች ውስጥ በሚስማሙበት መመዘኛ ሥር የ "√" ምልክት ያድርጉ፡፡

በ.ከ = በጣም ከፍተኛ　　መ = መካከለኛ　　በ.ዝ = በጣም ዝቅተኛ

ከ = ከፍተኛ　　ዝ = ዝቅተኛ

| ተ.ቁ. | ሐሳብ (ጥያቄ) | መመዘኛ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በ.ከ | ከ | መ | ዝ | በ.ዝ |
| 1 | በ11ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያላቸው ብቃት፣ | | | | | |
| 2 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የማዳበር ብቃት፣ | | | | | |
| 3 | ተማሪዎች በአማርኛ ክ/ጊዜ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት የንባብ ልምምድ፣ | | | | | |
| 4 | የተማሪዎች በአማርኛ መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ምንባቦች የማንበብ ፍላጎት፣ | | | | | |
| 5 | ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የመስራት ፍላጎት ምን ያህል ነው ? | | | | | |
| 6 | በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚጫወተው ሚና፣ | | | | | |
| 7 | ከሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ውስጥ በክፍል ውስጥ የማንበብ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ብዛት ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 8 | ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው ? | | | | | |
| 9 | የተማሪዎች በአማርኛ የተጻፉ የተለያዩ ጽሑፎችን የማንበብ ፍላጎት ምን ያህል ነው ? | | | | | |
| 10 | በአጠቃላይ ሲታይ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ያህል ነው ? | | | | | |

## ክፍል አራት፡

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሶችዎንና አስተያየቶችዎን በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ላይ ያስፍሩ፡፡

1. የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ነው የሚሉ ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስልዎታል ?

   ሀ. ______________________________

   ለ. ______________________________

   ሐ. ______________________________

   መ. ______________________________

   ሠ. ______________________________

2. የአማርኛ መማሪያ መጽሐፉ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ አያዳብርም የሚሉ ከሆነ ምክንያትዎን ይግለጹ፡፡

   ሀ. ______________________________

   ለ. ______________________________

   ሐ. ______________________________

   መ. ______________________________

   ሠ. ______________________________

3. የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ምን መደረግ አለበት ይላሉ ?

   ሀ. ______________________________

   ለ. ______________________________

   ሐ. ______________________________

   መ. ______________________________

   ሠ. ______________________________

አመሠግናለሁ ፡፡

አባሪ 2:- የምልከታ ዝርዝር /Observation sheet/

በ11ኛ ክፍል ውስጥ በሚካሄደው የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት ላይ ምልከታ /Observation/ ለማካሄድ የተዘጋጀ የመከታተያ ዝርዝር /Observation sheet/

ትምህርት ቤት: ______________________

መምህር: ______________________

| ተ.ቁ. | የመምህሩና የተማሪዎች ተግባራት | $ት_1$* | $ት_2$* |
|---|---|---|---|
| 1 | መምህሩ የምንባቡን ርዕስ ለተማሪዎች ይናገራል:: | | |
| 2 | መምህሩ የምንባቡን ርዕስ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጽፋል:: | | |
| 3 | መምህሩ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ አዳዲስ ቃላትን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጽፋል:: | | |
| 4 | መምህሩ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ አዳዲስ ቃላትን ፍችዎች ለተማሪዎች ይገልጻል:: | | |
| 5 | ተማሪዎች ስለምንባቡ መልዕክት ሐሳብ ይሰነዝራሉ:: | | |
| 6 | መምህሩ ለተማሪዎች ምንባቡን የሚያነቡበትን ዓላማ ይገልጽላቸዋል:: | | |
| 7 | መምህሩ ምንባቡን ድምፁን ከፍ አድርጎ ያለምንም ገለጻ (ማብራሪ) ያነባል:: | | |
| 8 | መምህሩ ድምፁን ከፍ አድርጎ ዐረፍተ ነገር በዐረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ በአንቀጽ እያብራራ (ገለጻ እየሰጠ) ያነባል:: | | |
| 9 | ተማሪዎች በፀጥታ ያነባሉ:: | | |
| 10 | ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ተራ በተራ ያነባሉ:: | | |
| 11 | ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሚያነቡበት ጊዜ(የሚያቡ ከሆነ) ሲሳሳቱ፣<br>11.1 መምህሩ ንባባቸውን በማቋረጥ ስህተቱን አስተካክሎ ያነበዋል::<br>11.2 አንባቢው ተማሪ ማንበቡን አቋርጦ እንዲያስተካክል በመምህሩ ይነገረዋል::<br>11.3 ተማሪው ማንም ጣልቃ ሳይገባበት ማንበቡን ይቀጥላል:: | | |
| 12 | ተማሪዎች ስለተነበበው ምንባብ በጥንድ ወይም በቡድን እርስ በርስ ይወያያሉ:: | | |
| 13 | መምህሩ የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ ለተማሪዎች ይገልጻል:: | | |
| 14 | ተማሪዎች ግልጽ ያልሆኑላቸውን ነጥብ መምህሩን ይጠይቃሉ:: | | |
| 15 | መምህሩ ተማሪዎችን የራሱን የቃል ጥያቄዎች ይጠይቃል:: | | |
| 16 | መምህሩ በቀጥታ በመጽሐፉ ውስጥ ወደሚገኙት መልመጃዎች ይሸጋገራል:: | | |
| 17 | የመልመጃዎችን ጥያቄዎች ተማሪዎች በቃል ይመልሳሉ:: | | |
| 18 | መምህሩ ጥያቄዎቹን በቤት ስራነት ለተማሪዎች ይሰጣል:: | | |

* $ት_1$ = ትምህርት አንድ * $ት_2$ = ትምህርት ሁለት

<u>አባሪ 3</u>፡- አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች

ሀ. ፈተና አንድ

ስም ከነአባት ________________

ፆታ ________________

ዕድሜ ________________

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ________________

<u>አጠቃላይ መግለጫ</u>፣ የዚህ ፈተና ዋነኛ ዓላማ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማጥናት ነው፡፡ በመሆኑም ምንባቡን በተቻለ መጠን በጥንቃቄና በተለመደው ፍጥነት ካነበብክ/ሽ/ በኋላ ከምንባቡ ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች በተሰጡት መመሪያዎች መሠረት መልስ/ሺ/፡፡

<u>ምንባብ</u>

የትምህርትን ጥራትና ጥልቀት ለማረጋገጥ ወሳኝ ናቸው ተብለው የሚጠቀሱ አንዳንድ ጉዳዮች አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የትምህርት ቤቶች በድርጅት መሟላት አንዱ ነው፡፡ የትምህርት ቤቶች በቤተመጻሕፍት፣ በቤተ ምርምሮችና በሌሎችም የትምህርት መሣሪያዎች መሟላት ለትምህርት ጥራትና ጥልቀት ያግዛል፡፡

የትምህርትን ጥራትና ጥልቀት ለማረጋገጥ በወሳኝነት ከሚጠቀሱት ጉዳዮች መካከል ሁለተኛው የልምድ እርዝማኔ ነው፡፡ በብዙ አካባቢዎች የረዥም ዓመታት ዕድሜ ያላቸው ትምህርት ቤቶች የትምህርት ጥራትና ጥልቀት እንዳላቸው ይገመታል፡፡ ይህም ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ እነዚህ ትምህርት ቤቶች የረዥም ዓመታት እድሜያቸው እራሳቸውን በድርጅት ለማሟላትና ለማጠናከር እንዲችሉ እረድቷቸዋል፡፡ ይህም ማለት አሰራራቸውን ለማሻሻል የተሻሻለውንም ለማጠናከር ልምድም እድልም ሰጥቷቸዋል፡፡

የሌሎች አገሮች የትምህርት ተቋሞችን በተነፃፀሮ መመልከትም የትምህርትን ጥራትና ጥልቀት ለማረጋገጥ እንደ ሶስተኛ ወሳኝ ጉዳይ የሚታይበት ጊዜም ጥቂት አይደለም፡፡ የሌሎች አገሮች የትምህርት ተቋሞች ምን እና እንዴት እንደሚያስተምሩ፣ የምዘና ስልታቸው እንዴት እንደሆነ፣ ወዘተ. መመልከቱ የራስን ድክመት ወይም

ብርታት ለመገመት ያስችላል፡፡ እንዲያውም በከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች መካከል የተማሪዎችና የመምህራን ልውውጥ በሚታሰብበት ወቅት ይህንን የመሰለው ንጽጽሮሽ ከባድ ሚዛን የሚሰጠው ሆኖ ይገኛል፡፡ ልውውጡ ተግባራዊ ይሁን ከተባለም የራስን ጥንካሬና ጥራት በሚቻል ሁሉ እንዲበልጥ እንጂ እንዳያንስ ትኩረት ይደረጋል፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የትምህርትን ጥራትና ጥልቀት ለማረጋገጥ ወሳኝነት አላቸው ቢባሉም መምህር ከሚጫወተው ሚና ጋር ሲነፃፀሩ ከፍተኛውን ሥፍራ አይዙም፡፡ ትምህርት ቤቶች ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ቢያሟሉም ጥራትና ብቃት ያላቸው መምህራን ከሌሉዋቸው የትምህርት ጥራትና ጥልቀት ሊጠበቅም ሊዳብርም አይችልም፡፡

ለትምህርት ጥራትና ጥልቀት መረጋገጥ መምህራን ይህን ከፍተኛ ሚና ለመጫወት የሙያቸው ባህሪ የሚያስገድዳቸው ቢሆንም ግዳጅን በሚገባ ለመወጣት ደግሞ የሚፈለጉባቸው ዝግጅቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ የሚያስተምሩትን ትምህርት ጠንቅቆ ማወቅ ነው፡፡ የሚያስተምሩትን ትምህርት ጠንቅቆ ማወቅም ምን አዲስ አስተሳሰብ ተጨምሯል? ምን አስተሳሰብ ተሽሯል? ምንስ ተጽፏል ወዘተ. ለሚሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ማግኘትን ያካትታል፡፡ ይህንን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ ካላሰለሰ ንባብና ምርምር ነው፡፡ ስለሆነም የዚህን አስፈላጊነትና ተገቢነት ለመምህራን መግለጽ "ለቀባሪ የማርዳት" ያህል ነው ፡፡

ሁለተኛው ከመምህራን የሚጠበቅ ያላሰለሰ ዝግጅት ሙያን የማዳበር ጉዳይ ነው፡፡ ሙያን የማዳበር ጉዳይ የማስተማርን ስልትና ጥበብ ከጊዜ ወደ ጊዜ ማሻሻልን ያጠቃልላል፡፡ ማስተማር ሳይንስም ጥበብም ነው፡፡ በሳይንስነቱ እንደ ሌሎቹ የሳይንስ ዘርፎች ሁሉ ጥናትና ምርምር እየተደረገበት ያረጁና ጠቃሚ ያልሆኑ ግኝቶች ይጣላሉ፡፡ አዳዲስና ጠቃሚ የሆኑ ግኝቶች ደግሞ ይገለጻሉ፡፡ በጥበብነት ባህሪዩም ቀጭጮ የሚቀር ሳይሆን እየተሻሻለና እያደገ የሚሄድ ነው፡፡ ስለዚህም መምህራን በዚህ ዘርፍ የሚጠበቅባቸው የሙያ ዝግጅት ከፍተኛ ነው፡፡

/ደወል፣ ገጽ 5 - 6/

<u>መመሪያ አንድ፡</u> ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት ምርጫዎች ውስጥ በምንባቡ መሠረት መልስ የሚሆነውን ምረጫ የሚያመለክተውን ሆሄ በመክበብ አመልክት (አመልክች)፡፡

1. ለምንባቡ ተስማሚ ርዕስ ሊሆን የሚችለው ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ነው ?
   ሀ. የመምህራን የሙያ ዝግጅትና ግዴታ
   ለ. የትምህርት ቤቶች የልምድ ልውውጥ
   ሐ. የትምህርት ጥራትና ጥልቀት
2. በአምስተኛው አንቀጽ ውስጥ "የዚህን አስፈላጊነት" የተባለው ምንድነው?
   ሀ. ለተለያዩ ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ማግኘት
   ለ. የማያቋርጥ ንባብና ምርምር ማካሄድ
   ሐ. የመምህራን ተልዕኮአቸውን በሚገባ መወጣት
   መ. ከመምህራን የሚጠበቁ ግዴታዎች
3. በስድስተኛው አንቀጽ ውስጥ "ቀጭጮ የሚቀር አይደለም" የተባለው ምንድን ነው?
   ሀ. ሳይንስ
   ለ. ጥበብ
   ሐ. ጥናትና ምርምር
   መ. ማስተማር
4. በመጨረሻው አንቀጽ ውስጥ "በዚህ ዘርፍ" ሲል ምን ማለቱ ነው ?
   ሀ. የማስተማር ሙያን በማዳበር ዘርፍ ማለቱ ነው ፡፡
   ለ. የማስተማር ሣይንስነትን በማረጋገጥ ዘርፍ ማለቱ ነው፡፡
   ሐ. የማስተማር ጥበብነትን በመገንዘብ ዘርፍ ማለቱ ነው፡፡
   መ. የማስተማር ሙያን በጥናትና ምርምር በማስደገፍ ዘርፍ ማለቱ ነው፡፡
5. የጽሑፉን አጠቃላይ መልዕክት የያዘው ዐረፍተ ነገር የሚገኘው በስንተኛው አንቀጽ ውስጥ ነው?
   ሀ. በአንደኛው
   ለ. በሁለተኛው
   ሐ. በሦስተኛው
   መ. በመጨረሻው

<u>***መመሪያ ሁለት***</u>፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልስ (መልሽ)።

1. ለትምህርት ጥራትና ጥልቀት ወሳኝ ናቸው ከሚባሉት ነጥቦች ውስጥ ሁለቱን ጥቀስ፡፡

   ሀ. ______________________________

   ለ. ______________________________

2. ረጅም ዕድሜ ያላቸው ትምህርት ቤቶች የትምህርት ጥራትና ጥልቀት እንዳላቸው የሚገመተው ለምንድን ነው ?

   ______________________________

   ______________________________

3. መምህራን ግዴጃቸውን በሚገባ ለመወጣት የሚጠበቁባቸው ዝግጅቶች ምን እና ምን ናቸው ?

   ሀ. ______________________________

   ለ. ______________________________

4. ለትምህርት ደረጃ መጠበቅ ከሚያስፈልጉ ጉዳዮች ሁሉ ከፍተኛውን ሚና የሚጫወተው ______________________________ ነው፡፡

5. የአንድን ትምህርት ቤት (ተቋም) ጠንካራና ደካማ ጎን ለመመዘን የሚቻለው በምን ዘዴ ነው ?

   ______________________________

   ______________________________

ለ. ***ፈተና ሁለት***

ስም ከነአባት ____________________

ፆታ ____________________

ዕድሜ ____________________

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ____________________

**አጠቃላይ መግለጫ፡** የዚህ ፈተና ዋነኛ ዓላማ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማጥናት ነው፡፡ በመሆኑም ምንባቡን በተቻለ መጠን በጥንቃቄና በተለመደው ፍጥነት ካነበብክ (ካነበብሽ) በኋላ ከምንባቡ ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች በተሰጡት መመሪያዎች መሠረት መልስሰ (መልሽ)፡፡

**ምንባብ**

ቃላት የአንድ ቋንቋ ሥርዓት በሚፈቅደው ቅደም ተከተል መሠረት ተገጣጥመው መልዕክት ለማስተላለፍ የሚያገለግሉ የዐረፍተ ነገር መሠረታዊ መለዋወጫ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ዐረፍተ ነገሩ በቃል ምክንያት ሲበላሽ ብልሽት ያስከተለውን ቃል አስወጥቶ አዲስ ቃል በማስገባት ዐረፍተ ነገሩ ተጠግኖ የተፈለገውን ትክክለኛ መልዕክት እንዲያስተላለፍ ይደረጋል፡፡ መልዕክቱን ለማስተላለፍ የሚያገለግሉት ቃላትም አጠቃላይ ወይም ዝርዝር ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዚህ አንፃር ቃላት ከገንዘብ ጋር ይመሳሰላሉ፡፡ ገንዘብ ተዘርዝሮ ልዩ ልዩ ጉዳይን ለመፈፀም እንደሚረዳ ሁሉ አጠቃላይ የሆነው ቃልም ወደ ዝርዝር ቃላት ተለውጦ ተፈላጊውን መልዕክት እንዲያስተላልፍ ይደረጋል፡፡ ለዚህም ቃላትን ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

የሰው ልጅ የተፈለገውን መልዕክት ለማስተላለፍ የሚያስችሉትን ቃላት የሚያውቅባቸው የተለያዩ ዘዴዎች አሉ፡፡ ከዘእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ማዳመጥና ማንበብ ናቸው፡፡ አንድ ሰው የቋንቋው ተናጋሪዎች ሲናገሩ በማዳመጥ የተለያዩ ጽሑፎችንም በማንበብ የቃላት ችሎታውን ያዳብራል፡፡

ከዚህ በላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም ዘዴዎች አማካኝነት የሚታወቁት ቃላት ከሚያገለግሉበት ሁኔታ አንፃር የመነጋገሪያ እና የመጻፊያ ወይም የማንበቢያ ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ የመጀመሪያዎቹ በቋንቋው መናገር የሚችል ሰው በንግግር

የሚጠቀምባቸው ናቸው፡፡ በሁለተኛው ክፍል ሥር የሚካተቱት ደግሞ ሐሳብን በጽሑፍ ለመግለጽ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ የተለያዩ ጽሑፎችን ለማንበብ ቃላት ከሚያገለግሉበት ሁኔታ አንፃር በሁለት ይከፈላሉ ቢባልም በአንዱ ሥር የሚካተቱት በሌላኛውም ሊጠቃለሉ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ለመነጋገሪያ የሚያገለግሉት ለመጻፊያ ወይም ለማንበቢያ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

ቃላት በአገልግሎት ላይ ከሚውሉበት የጊዜ መጠን አኳያ ደግሞ የዘወትር መገልገያና የአልፎ አልፎ መገልገያ ተብለው ይከፈላሉ፡፡ የዘወትር መገልገያ የሚባሉት በየዕለቱ በአገልግሎት ላይ የሚውሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም አብዛኛውን ጊዜ አይረሱም፡፡ የአልፎ አልፎ መገልገያ የሚባሉት ደግሞ አንዳንዴ ካልሆነ በስተቀር በየዕለቱ በአገልግሎት ላይ አይውሉም፡፡ በዚህም ምክንያት ብዙ ጊዜ ይረሳሉ፡፡

ምንጭ፣ በስቴንስል ከተባዛ የርቀት ትምህርት የአማርኛ ማስተማሪያ ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡

<u>መመሪያ አንድ</u>፣ ከዚህ በታች ለቀረቡት አምስት ጥያቄዎች ለእያንዳንዳቸው ከተሰጡት ምርጫዎች መካከል ከምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ የሚያመለክተውን ሆሄ በመምረጥ ክበብ (ክበቢ)፡፡

1. ከሚከተሉት ውስጥ የመጀመሪያው አንቀጽ ፍሬ ሀሳብ የትኛው ነው ?
   ሀ. የቃላት አገልግሎት
   ለ. ዐረፍተ ነገርን ማስተካከል
   ሐ. የቃላት ቅደም ተከተል
   መ. የቋንቋ ሥርዓታዊነት
2. የተዛባ ዐረፍተ ነገር ተስተካክሎ የተፈለገውን መልዕክት እንዲያስተላልፍ የሚደረገው እንዴት ነው ?
   ሀ. ዐረፍተ ነገሩን በቋንቋው ስርዓት መሠረት በመጻፍ
   ለ. በዐረፍተ ነገሩ ውስጥ ያሉትን ቃላት ቅደም ተከተል በማስተካከል
   ሐ. ብልሽት ያስከተለውን ቃል በሌላ ተስማሚ ቃል በመተካት
   መ. አጠቃላይ የሆነውን ቃል ወደ ዝርዝር ቃላት በመተንተን

3. ቃላት እና ገንዘብ የተነፃፀሩት ከ __________ አኳያ ነው፡፡
   ሀ. ከመጠናቸው አነስተኛነት
   ለ. ተመንዝረው ለተፈለገው አገልግሎት ከመዋላቸው
   ሐ. አጠቃላይ ወይም ዝርዝር ከመሆናቸው
   መ. ልዩ ልዩ ጉዳይን ለመፈፀም ከማገልገላቸው
4. ቃላት የመነጋገሪያና የመጻፊያ (የማንበቢያ) ተብለው የሚከፈሉት ከምን አንጻር ነው?
   ሀ. በአገልግሎት ላይ ከሚውሉበት የጊዜ መጠን
   ለ. ከመረሳታቸው ወይም አለመረሳታቸው
   ሐ. ከሚታወቁበት ወይም ከሚጠኑበት
   መ. በአገልግሎት ላይ ከሚውሉበት ሁኔታ
5. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ በመጨረሻው አንቀጽ ውስጥ ተብራርቷል፡፡
   ሀ. የቃላት አሰባሰብ
   ለ. የቃላት አመዳደብ
   ሐ. የቃላት አስፈላጊነት
   መ. የቃላት አይረሴነት

<u>መመሪያ ሁለት፣</u> ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶችን በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ላይ ጻፍ (ጻፊ)፡፡

1. ቃላት መልዕክት ለማስተላለፍ የሚችሉት በዐረፍተ ነገር ውስጥ በምን መሠረት ሲገጣጠሙ ነው ?
   ______________________________________________
2. አንድ አጠቃላይ የሆነ ቃል ወደ ዝርዝር ቃላት የሚለወጠው ለምንድን ነው?
   ______________________________________________
3. ከቃላት ማወቂያ መንገዶች ውስጥ ሁለቱን ጥቀስ (ጥቀሽ)፡፡
   ሀ. ______________________________________
   ለ. ______________________________________
4. የሰው ልጅ የሚያውቃቸው ቃላት በአገልግሎት ላይ ከሚውሉበት የጊዜ መጠን አንፃር በስንት ይመደባሉ ?
   ______________________________________________
5. የተወሰኑ ቃላት የማይረሱበት ምክንያት ምንድን ነው ?
   ______________________________________________

አባሪ 4:- ልዩ ልዩ ስሌቶች

### ሀ. የፈተናዎች አስተማማኝነት

$$r = \frac{n[Sd^2_{x2} - (sd^2_{y1} + sd^2_{y2})]}{Sd^2_{x2}}$$

$n = 2$

$Sd^2_{x2} = 17.55$

$Sd^2_{y1} = 3.97$

$sd^2_{y2} = 6.4$

$$r = \frac{2\ [17.55 - (3.97 + 6.4)]}{17.55}$$

$$r = \frac{2[17.55 - 10.37]}{17.55}$$

$$r = \frac{14.36}{17.55}$$

$$= 0.82$$

### ለ. የፈተናዎች ውጤት ዝምድና /ግንኙነት/

(pearson product moment correlation)

$$pr = \frac{N\ \Sigma\ xy - (\Sigma\ x)\ (\Sigma y)}{\sqrt{N\Sigma x^2 - (\Sigma x)^2\ x\ \ N\Sigma y^2 - (\Sigma y)^2}}$$

$N = 40$

$\Sigma x = 210$

$\Sigma x^2 = 1328$

$(\Sigma x)^2 = 44100$

$\Sigma y = 221$

$\Sigma y^2 = 1417$

$(\Sigma x)^2 = 48841$

$\Sigma xy = 1334$

$$pr = \frac{40 \times 1334 - 210 \times 221}{\sqrt{40 \times 1328 - 44100 \times 40 \times 1417 - 48841}}$$

$$= \frac{53360 - 46410}{\sqrt{9020 \times 7839}}$$

$$= \frac{6950}{8408.64}$$

$$= 0.83$$

## ሐ. <u>የፆታና አንብቦ የመረዳት ዝምድና ስሌት</u>

$$t\ cal = \frac{\bar{x}_1 - \bar{x}_2}{\sqrt{S^2p\ (1/N_1 + 1/N_2)}}$$

**ሴት ተጠኚዎች**

$N_1 = 99$

$\bar{X}_1 = 5.54$

$Sd_1 = 1.84$

**ወንድ ተጠኚዎች**

$N_2 = 121$

$\bar{X}_2 = 5.26$

$Sd_2 = 2.06$

$$S^2p = \frac{(N_1 - 1)(Sd_1)^2 + (N_2 - 1)(Sd_2)^2}{N_1 + N_2 - 2}$$

$$S^2p = \frac{(99 - 1)(1.84)^2 + (121 - 1)(2.06)^2}{99 + 121 - 2}$$

$$= \frac{331.79 + 509.23}{218}$$

$$= \frac{841.02}{218}$$

$$= 3.86$$

$$t\ cal = \frac{5.54 - 5.26}{\sqrt{3.86(1/99 + 1/121)}}$$

$$= \frac{0.28}{0.266}$$

$$= 1.052$$

መ. <u>የአፍ መፍቻ ቋንቋ እና አንብቦ የመረዳት ዝምድና ስሌት</u>

$$t\ cal = \frac{\bar{x}_1 - \bar{x}_2}{\sqrt{S^2p(1/N_1 + 1/N_2)}}$$

$$S^2p = \frac{(N_1 - 1)(Sd_1)2 + (N_2 - 1)(Sd_2)2}{N_1 + N_2 - 2}$$

<u>በአማርኛ አፍ የፈቱ፡</u>

$N_1 = 151$

$\bar{X}_1 = 5.54$

$Sd_1 = 2.04$

<u>በአማርኛ አፍ ያልፈቱ፡</u>

$N_2 = 69$

$\bar{X}_2 = 5.05$

$Sd_2 = 1.75$

$$S^2p = \frac{(151 - 1)(2.04)^2 + (69 - 1)(1.75)^2}{151 + 69 - 2}$$

$$= \frac{624.24 + 208.25}{218}$$

$$= \frac{832.49}{218}$$

$$= 3.82$$

$$t\ cal = \frac{5.54 - 5.05}{\sqrt{3.82\ (1/151 + 1/69}}$$

$$t\ cal = \frac{0.49}{0.294}$$

$$= \underline{1.725}$$

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተገለፀውና የፈረምኩት፣ ይህ ጥናት የራሴ ስራ መሆኑን፣ በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ጽሑፎችና ምንጮችም በሙሉ የጠቆምኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ::

ስም:- ማስተዋል ውበቱ

ፊርማ:- ________

አድራሻ:- አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ::

ቀን :- ግንቦት 15 1989 ዓ.ም.